# አዲስ ዘመን

እፎይ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 018 መስከረም 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “ሀገር በተደፈረች ጊዜ ሕመሙን እየቻለ ግንባር ተገኝቶ ሠራዊቱን አጀግኗል፣ ሠልጣኞችንም አበርትቷል”



\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማቸውን ኃዘን ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማቸውን ኃዘን ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በማረፉ የተሰማኝ ኃዘን ከባድ ነው ብለዋል በኃዘን መልዕክታቸው።

ለሀገሩ በአጭር እድሜው ብዙ የሠራ ከያኒ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ሀገር በተደፈረች ጊዜ ሕመሙን እየቻለ ግንባር ተገኝቶ ሠራዊቱን አጀግኗል፣ ሠልጣኞችንም አበርትቷል ሲሉ ለሀገር ያበረከተውን አስተዋጽዖ ዘክረዋል፡፡

የባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ አቀንቃኙ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ትናንት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

አርቲስቱ ባደረበት ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ሕይወቱ ማለፉን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከቅርብ ወዳጆቹ ያገኘው መረጃ ያመለክታል። ኢቢሲ ከአዲስ አበባ ፖሊስ የተገኘ መረጃን ጠቅሶ እንደዘገበው አርቲስቱ ትናንት ጠዋት ሕመም ተሰምቶት ለሕክምና በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ወደሚገኝ አንድ የሕክምና ማዕከል ገብቶ ሕክምና

“ሀገር በተደፈረች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










አቶ ብርሃነ ተስፋይ

# አሸባሪው ትሕነግ እንደሚጠፋ በመገንዘቡ ሕዝቡን ይዞ ለመጥፋት እየሠራ መሆኑን ትሕዴን ገለጸ

**መሰረት ገ/ዮሐንስ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ እንደሚጠፋ ስለሚያውቅ ሕዝብ ይዞ ለመጥፋት እየሠራ ነው ሲል የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲ ንቅናቄ (ትሕዴን) የወታደራዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ብርሃነ ተስፋይ ገለጹ፡፡

አቶ ብርሃነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤

አሸባሪው ትሕነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሽብር ቡድኑን ወደስልጣን ስመመለስ የሚጥሩ የውጭ ሚዲያዎችን ፕሮፖጋንዳ በቅንጅት መመከት ይገባል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- እውነቱን እያወቁ የአሸባሪውን ትሕነግ መረጃ ብቻ በመውሰድ የሚቀባበሉና ቡድኑን ዳግም ወደስልጣን ለመመለስ የሚሯሯጡ አንዳንድ የውጭ ሚዲያዎች የፕሮፖጋንዳ ዘመቻን በቅንጅት መመከት እና መቀልበስ እንደሚገባ የሕግ ምሑር ተናገሩ፡፡

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ዲን አቶ ዓለሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አንዳንድ ውጭ ኃይሎች የሀገራቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት አሸባሪው ትሕነግ ትዕዛዝ አስፈጻሚ በመሆኑ ቡድኑን ወደስልጣን ለመመለስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡

በዚህ የተነሳ በየሚዲያዎቻቸው ሳይቀር የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ድጋፍ እያደረጉለት ይገኛሉ ያሉት አቶ ዓለሙ፤ በመሆኑም በአሸባሪው ትሕነግ የሚጋለቡ እነዚህ የውጭ ሚዲያዎች ፕሮፖጋንዳን ለመቀልበስ በቅንጅት መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ዓለሙ ገለጻ፤ አሸባሪው ትሕነግ በተለያዩ አካባቢዎች ያደረሰው ግፍ ለውጭ ኃይሎች ስውር



አቶ ዓለሙ ታዬ

አይደለም፡፡ ሆኖም ሀገራቱ ቅድሚያ የሚሰጡት የሀገራቸውን ጥቅም ማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም የዓለም አቀፍ የጦርነት ሕግ የማይፈቅዳቸውን ነገሮች በሙሉ ለመሸፋፈን እየሞከሩ ነው፡፡

ትሕነግ በሀገሪቱ ሥልጣን ባለው አካል በሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀ ቡድን መሆኑም ሆነ በጦርነት ወቅት በተለይ ንፁሐን ዜጎች ላይ ያደረሰው ግፍ በእነዚህ ኃይሎች ሚዛን ከሀገራቸው

የሽብር ቡድኑን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ‹‹ኢትዮጵያ የገጠሟትን ፈተናዎች በድል እንድትወጣ ስመከላከያ ሠራዊት የሚደረገውን ድጋፍ አጠናክረን እንቀጥላለን››

\- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የገጠሟትን ፈተናዎች በድል እንድትወጣ ለመከላከያ ሠራዊት የሚደረገውን ሁለንተናዊ የደጀንነት ሚና አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ-ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን የመስቀል በዓልን ምክንያት በማድረግ በጦር ኃይሎች ሆስፒታል በመገኘት ለአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ማዕድ አጋርቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ በዚህ ወቅት እንዳሉት፤ ለሕዝብ ሰላም እና የአገር ሉዓላዊነት ከሚዋደቅ ሠራዊት ጋር በዓልን ማሳለፍ ከክብር በላይ ክብር ነው።

የማዕድ ማጋራቱ መከላከያ ሠራዊቱ ከሚከፍለው ዋጋ ጋር የሚስተካከል ሆኖ ሳይሆን ለሠራዊቱ

‹‹ኢትዮጵያ የገጠሟትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ኮርፖሬሽኑ በዘንድሮው ዓመት ከ380 ሺ በላይ ኩንታል የስንዴ ዘር ለማባዛት እቅድ ይዟል

ገጽ 2

# በአዲስ አበባ የመስቀል ደመራ በዓል ከምንጊዜውም በላይ በሰላም ተጠናቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመስቀል ደመራ በዓል በከተማዋ ከ2 ሺህ 200 ቦታዎች በላይ ከምንጊዜውም በላይ በደመቀና ባማረ ሁኔታ ትውፊቶቹንና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ በሰላም ተከብሮ መጠናቀቁን ገለጸ።

የከተማ አስተዳደሩ የመስቀል በዓልን በሰላም መጠናቀቅ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፤ ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ በዓሉ የጋራ በዓላችንና ኢትዮጵያን ለዓለም ያስተዋወቀ ነው በማለት በዓሉ ከሃይማኖታዊ ገጽታው ባሻገር የኢትዮጵያ መልካም ገጽታ መገለጫና የኢትዮጵያ ሰላም ወዳድነት ማሳያ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል ብሏል፡፡

ነዋሪው በአብሮነት ለደመራውና ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማዘጋጀት አካባቢውን በማስዋብ ድንቅ ኢትዮጵያዊ እሴት ጎልቶ እንዲወጣና ከተማችን የኅብረብሔራዊነትና የመተባበር ተምሳሌት መሆኗን አሳይቷል ብሏል አስተዳደሩ በመግለጫው፡፡

እንዲሁም የፀረ ሰላም ኃይሎች የበዓሉን ድባብ ለማጥፋት የሀገራችንን ገፅታ ለማበላሸት የሞት የሽረት ትንቅንቅ ያደረጉበትና አዲስ አበባን የሽብር ማዕከል ለማድረግ ብዙ ሃብት አፍስሰው የሰው ኃይል አሰማርተው ከበዓሉ ቀደም ብለው ሲዘጋጁበት የነበረው የሽብር እቅዳቸው በሕዝቡና በፀጥታ ኃይሉ ትብብር ምኞታቸው ቅዠት ሆኖ መቅረቱን ገልጿል መግለጫው፡፡

በዚህም ፀረ ሰላም ኃይሎችን አጋልጦ በመስጠት በርካታ ተላላኪዎችና ለሽብር ድርጊት ሊውሉ የተዘጋጁ መሣሪያዎች ጭምር በየአካባቢው በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስተዳደሩ አስታውቋል፡፡

የልዩነትና የመከፋፈል አጀንዳዎችን በማስወገድ በንቃትና በትጋት በአንድነት ተናበንና ተዋህደን ዘላቂ ሰላማችንን ልናረጋግጥ ብሎም እነዚህን ኃይሎች እስከ መጨረሻው ተስፋ ልናስቆርጥ ይገባል ብሏል አስተዳደሩ በመግለጫው።

ፀረ ሰላም ኃይሎች ምንም ቢተባበሩና የፈለገውን ያህል ቢዘጋጁ ከሕዝባችንና ከፀጥታ ኃይላችን ዐይንና ጆሮ የማያመልጡና ለዘላቂ ሰላማችን ስጋት ሊሆኑ እንደማይችሉ በጉልህ ያረጋገጥንበት በዓል ነውም ብሏል አስተዳደሩ፡፡

በመስቀል አደባባይ እና በየአካባቢው የመስቀል ደመራ በዓል በደማቅና ሰላማዊ ሁኔታ ሃይማኖታዊ እሴቱንና ሥርዓቱን ከፍ አድርጎ ተከብሮ እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት ከተማ አስተዳደሩ አመስግኗል፡፡

ለመጪው የኢሬቻ በዓል ትብብራችንና አንድነታችንን ጠብቀን ሳንዘናጋ እጅ ለእጅ ተያይዘን ከተማችንን ዳግም የሰላም አምባ ለማድረግ እንድንነሳ ሲልም ጥሪ አቅርቧል፡፡

በተለይም የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን በተለመደው የእንግዳ ተቀባይነት፣ የወንድማማችነትና እህትማማችነት መንፈስ ተቀብለን በማስተናገድ፣ ፍቅራችንን በማጋራት በአብሮነታችን የኢትዮጵያን ከፍታ ዳግም ልናረጋግጥና የጠላትን ሴራ በአደባባይ ዳግም ልናከሽፍ ይገባል ብሏል መግለጫው፡፡

# ኮርፖሬሽኑ በዘንድሮው ዓመት ከ380 ሺ በላይ ኩንታል የስንዴ ዘር ለማባዛት እቅድ ይዟል



አቶ ፈለቀ ገዛኸኝ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው ዓመት ከአስራ አራት ሺ በላይ በሆነ ሄክታር መሬት ላይ ከ380 ሺ በላይ ኩንታል ምርጥ የስንዴ ዘር ለማባዛት እቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ኦፕሬሽናዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፈለቀ ገዛኸኝ እንደገለጹት፤ በመንግሥት ትልቅ እቅድ የተያዘበት የመስኖ ስንዴ እህል የማባዛት ሥራ በስፋት እየተከናወነ ነው። በዘንድሮው ዓመት በአስራ አራት ሺ 140 ሄክታር መሬት ላይ ሶስት መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺ ኩንታል ምርጥ የስንዴ ዘር ለማባዛት እቅድ ተይዟል። ከተባዛ በኋላ ወደ 20 ሺህ ሄክታር ለሚሸፍን መሬት የዘር ግብዓት ይሆናል። ከዚህ ውስጥ በአዋሽ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ወደ አራት መቶ ሄክታር መሬት ላይ እያባዛን ሲሆን አስር ሺ ኩንታል የሚጠጋ የስንዴ ምርት እንደሚገኝም ገልጸዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በፊንታሌ አንድ፣ ሁለትና አሚባራ እየተባዙ ያሉት ለቆላማ አካባቢ የሚሆኑ አዳዲስ ዝርያዎች ናቸው። ዝርያዎች እ.ኤ.አ በ2017 የወጡ ሲሆኑ ከፍተኛ ምርት ያስገኛሉ፤ ከምርምር ጣቢያዎች በመውሰድ 60 ሄክታር የሚደርስ መሬት ላይ በመሥራች ደረጃ ዘሩ እየተባዛ ነው። በቀጣይ አንድ ዓመት ተጨማሪ የማባዛት ሥራ በመሥራት ለአርሶ አደሮች የሚከፋፈል ይሆናልም ብለዋል።

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኮርፖሬሽንና የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በአንድ ሆልዲንግ ውስጥ ናቸው። በሆልዲንጉ ውስጥ ያሉ ሀያ ሰባት ድርጅቶችን በጋራ ለመሥራት በአዲስ መልክ ሥራ ጀምረዋል ብለዋል ዳይሬክተሩ። እንዲሁም በአዲስ መልክ እየለሙ ባሉ ኦሞ አንድ፣ተንዳሆና በለስ ላይ ኮንትራትም ወስደን በልዩ ሁኔታ በስፋት ዘር ለማባዛት በቅድመ ዝግጅት ላይ እንገኛለን። በነባሮች የዘር ማባዣ ላይ ስንዴና በቆሎን በስፋት ለመሥራት ዝግጅት እያደረግን ነው ሲሉም ገልጸዋል።

የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሁሉንም ግብዓት በአንድ መስኮት የሚያቀርብ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ስንዴን በማባዛት ላሉ አካላት ከመሬት ልማት ጀምሮ እስከ አጨዳ ድረስ ያሉትን ሥራዎች እናግዛለን። እንዲሁም ማዳበሪያና ዘር ከማቅረብ ጀምሮ የባለሙያ ድጋፍ በማድረግ ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘር እንዲደርስ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው። በጋራ ከሠራን እንደ መንግሥት የሚጠበቅብንን ኃላፊነት እንወጣለን፤ በተለይ ለአርሶ አደሩ በቂ ምርጥ ዘር እናቀርባለን። እንደ ሀገር ብዙ ያልሞከርናቸውና ለቆላማ አካባቢ የሚስማማ ዘር ማቅረብ ችግር ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቆላማ አካባቢዎች የሚመቹና የሚስማሙ ዘሮችን የማባዛት ሥራ ላይ ተሠማርተናል፤ ይህም የተሻለ ምርትን እንድናገኝ ያስችለናል ሲሉ ዳሬክተሩ ገልጸዋል፡

# የእንቁላል ፍላጎትና አቅርቦትን ለማመጣጠን እየሠራ መሆኑን ሚኒስቴሩ አስታወቀ

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፤ የእንቁላል ፍላጎትና አቅርቦትን ለማመጣጠን ኮኮክ የተሰኘውንና ጥምር ጠቀሜታ ያለውን የዶሮ ዝርያ ተጠቅሞ እየሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ዳይሬክተር ወይዘሮ ጽጌሬዳ ፈቃዱ እንዳስታወቁት፤ አሁን ያለውን የእንቁላል አቅርቦትና ፍላጎት ለማመጣጠን ኮኮክ የተሰኘውንና ጥምር ጠቀሜታ የሚሰጠውን የዶሮ ዝርያ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው።

የእንቁላል ገበያውን ንረት ለማርገብና የአቅርቦት ችግሩንም ለመፍታት በሚኒስቴሩ ከሚከናወኑት ተግባራት አንዱ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሯ፤ የዶሮ ዝርያው ሥጋ ብቻ ሳይሆን እስከ 180 እንቁላል መስጠት የሚችልና ከውጪ የመጣ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ነው።

በደብረ ዘይት ግብርና ምርምር ማዕከል ተሞክሮ ውጤታማነቱ ተረጋግጧል፤ አርሶ አደሩ ጋር በሚደርስበት ጊዜም እስከ 50 በመቶ ያህል ምግቡን ጭሮ በመብላት ለዶሮ ምርት ከሚወጣው የመኖ ወጪ ግማሽ ያህሉን እንዲቀንስ እንደሚያስችልም ገልጸዋል። ከዶሮ ዝርያው እንቁላሎቹን ለማስፈልፈል ምቹ መሆኑንና ሌሎች ዶሮዎች ከሚሰጡት እንቁላል እንደሚለይም አስረድተዋል።



ወይዘሮ ጽጌሬዳ ፈቃዱ

በዶሮ እርባታ ሥራ 70 ከመቶው ወጪ ለመኖ የሚወጣ መሆኑን ያስታወሱት ዳይሬክተሯ፤ ይሄን የዶሮ ዝርያ በመጠቀም የመኖ ዋጋ ይቀንሳል። ባለፈው 2014 ዓ.ም 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን እንቁላል መመረቱን ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ በተያዘው 2015 ዓ.ም እስከ 3 ነጥብ 6 ቢሊዮን እንቁላል ለማምረት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ ሀገር በእንቁላል አቅርቦትና ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ ፍላጎትና አቅርቦቱን በማመጣጠን ችግሩን ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ10 ዓመቱን መሪ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ካሉት ምርቶች 10 የሚሆኑት መለየቱንና በትኩረት እንዲሠራባቸው ማድረጉን እንቁላልም ከተለዩትና ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ዋናው መሆኑን አመልክተዋል።

እንደ ሀገር እንቁላል የመመገብ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን የጠቆሙት ወይዘሮ ጽጌረዳ፤ በዓመት አንድ ሰው 36 እንቁላል መመገብ ደረጃ ላይ መድረስ መቻሉን ጠቅሰዋል። ሆኖም የዓለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት አንድ ሰው በዓመት 180 እንቁላል መመገብ ይኖርበታል። እንደ ሀገር ይህን ለማሳካት ጥረቶች መደረግ እንዳለባቸው ገልጸዋል። ክፍተቱን ለመሙላትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉልና በሲዳማ ክልሎች እስከ ከፍተኛ የእንቁላል መጠን የሚሰጡትን የኮኮክ ዶሮ ዝርያዎችን የማባዛት ሥራ በስፋት እየተከናወነ መሆኑን አብራርተዋል ።

በሥራው ወጣቶችን፤ እናቶችንና የተለያዩ ባለሀብቶችን ጨምሮ በምርቱ ላይ መሠማራት ከሚገባቸው 60 በመቶ የሚደርሱ ኅብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ መቻሉንም ተናግረዋል። በዚህ መልኩ ምርቱ መስፋቱ ፍላጎቱና አቅርቦቱን ከማመጣጠን ባሻገር አሁን ላይ ያለውን የእንቁላል ገበያ ንረት የማረጋጋትና የኅብረተሰቡንም እንቁላል የመመገብ ባህል የማሻሻል ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

ዜና

# ሚኒስቴሩ ባለፈው በጀት ዓመት ከሆርቲካልቸር ዘርፍ 628 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አገኘ

- በ2015 በጀት ዓመት ከ770 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል



**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የግብርና ሚኒስቴሩ በ2014 በጀት ዓመት በሆርቲካልቸር ዘርፍ 628 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን አስታወቀ። በ2015 በጀት ዓመት ከ770 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል።

በግብርና ሚኒስቴር የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብደላ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ለሆርቲካልቸር ዘርፍ የሚፈልገውን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የአሠራርና ከፖሊሲ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥራዎችን እየተሠሩ ነው። ከተሠሩት ሥራዎች መካከል በተለያየ ቦታ በተበታተነ መልኩ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረውን በግብርና ሚኒስቴር ስር በማምጣት፣ በዘርፉ ለሚሠማሩ ባለድርሻ አካላት ተገቢ አገልግሎት ላይ የማሻሻያ ሥራው ተጠናቆ በ2015 እቅድ ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

አትክልት፣ መዓዛማ የሆኑ እጽዋቶች፣ ፍራፍሬ፣ቡና ሻይ፣ ቅመማቅመም፣ እንሰትና አበባ ልማት ዘርፉ ከተካተቱ መካከል እንደሆኑ የጠቀሱት አቶ አብደላ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሆርቲካልቸር ልማት የመስኖ ልማት መስፋፋትን ተከትሎ የመሬት መጠኑ እየጨመረ ነው። ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ዝርያዎችንና ሌሎች ግብዓችን በመጠቀም ረገድ ለውጦች አሉ ብለዋል።

እንደ አቶ አብደላ ገለጻ፣ በ2014 በሆርቲካልቸር ዘርፍ 589 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 628 ሚሊዮን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን ይህም ከእቅዱ በላይ ነው። ከዚህም ውስጥ ኢትዮጵያ ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ የምትገኝበት የአበባ ልማት 541 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ በማስገኘት ቀዳሚው ነው። ለውጤቱ መሳካት ድጋፍና ክትትል በማድረግ በየጊዜው ድክመቶችን በመለየት ለውጤታማነት በመሠራቱ ነው።

በ2015 በጀት ዓመት በዘርፉ ከ770 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት መታቀዱን የገለጹት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፣ ይህም የመልማት አቅምን ታሳቢ ያደረገ ነው። እቅዱን ለማሳካት በየደረጃው ካሉ አስፈጻሚ አካላትና አምራቾች ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ የሚፈልጉትን አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ በቅልጥፍና በመስጠት ግቡን ለማሳካት ታቅዷል ብለዋል።

እንደ አቶ አብደላ፣ ዘርፉ ውስን የሆነ የመሬት አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ውስንነት ችግሮች አሉበት። እነዚህን ችግሮች ቀርፎ መሥራት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል ብለዋል።

## በትግራይ የሞት ደብዳቤ ያክል የምትፈራው ፎርም

**ጌትነት ተስፋማርያም**

በትግራይ ክልል አህፈሮም ወረዳ ተወላጅ የሆነው ብርሃነ ኃይሌ አርሶአደር አባቱን እያገዘ ሠርቶ መለወጥን ምኞቱ አድርጎ ነበር፤ ግና ምኞቱን መና ሊያስቀርበት የሚችል አደጋ ከፊቱ ሲደቀን ኃዘን ውስጡን እርብሽብሽ አድርጎት እንደነበር አይዘነጋውም።

የኃዘኑ መነሾ ደግሞ የአሸባሪው ትሕነግ ታጣቂ መልማዮች ዓይናቸው እርሱ ላይ የማሳረፋቸው ምክንያት ነበር። ለአምስት ወራትም ከቤቱ ሳይወጣ እየተደበቀ ከትሕነግ መልማዮች ማምለጡን ይናገራል።

ታጣቂ መልማዮቹ ግን ጉዳያቸው የትግራይን ወጣት ማጥፋት ነበርና የብርሃነን የተስፋ ብርሃን ሊያጨልሙ በአንዲት በተረገመች ቀን ቤታቸው ድረስ ሰተት ብለው ሄዱ።



ፎቶ - ዳኜ አበራ

የሃፈሮም ወረዳ ወጣት ብርሃነ ሀይሌ

ያኔ አባቱ ልጃቸውን ለጦርነት መላክ እንደማይፈልጉና አብሯቸው እንደሚቆይ ቢናገሩም ሰሚ እንዳልነበራቸው ብርሃነ ያስታውሳል። የሽብር ቡድን መልማዮችም አባቱን አስረው ልጅህን በጦርነት እንዲሳተፍ ካልሰጠክ አምስት ሺህ ብር ትቀጣለህ የሚል የግዴታ ፎርም አምጥተው እንዳስፈረሟቸው ብርሃነ ኃዘን በተሞላበት ስሜት ሆኖ ድርጊቱን ያስታውሳል፡፡

ያቺን “የሞት ደብዳቤ” ያክል የምትፈራ የግዴታ ፎርም ደግሞ በትግራይ ገጠራማ አካባቢዎች የሚገኙ በርካታ ወላጆች እንባ እየተናነቃቸው መሙላታቸውን የሚገልጸው ብርሃነ፣ እናቶች እያለቀሱ የአብራኮቻቸውን ክፋይ ወደማይፈልጉት ጦርነት ሲልኩ መመልከቱን ተናግሯል።

በርካቶች በዚች የወላጅን ልብ በምታደማ ፎርም የተነሳ ኃዘን ቤታቸውን እንደወረረው ብርሃነ ትግራይ ክልል በነበረበት ወቅት መታዘቡን ያስረዳል።

መጥፎ ዕጣው ግን ከነብርሃነም ቤት መግባቱ አልቀረም። አባቱ ፎርሙ ላይ በገንዘብ ከፈረሙ በኋላ እምቢ ብሎ ቤቱ ቢቀር አርሶአደር አባቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ስቃይ ጠንቅቆ የተረዳው ልጅ ጭንቅ ጥብብ ብሎት እንደነበር ያስታውሳል፡፡

አባትም ልጄ ምን ይሻላል ብሩም በእጄ የለም ብለው በኃዘን ስሜት አቀርቅረው እንደቀሩ ይናገራል።

አባቱ ገንዘቡን መክፈል ካልቻሉ እንደሚሰቃዩና እንደሚገደሉ ገብቶታልና እርሳቸውን ለማዳን ሲል ብቻ ወደስልጠና መግባቱን ገልጿል።

በሰኔ ወር 2014 ዓ.ም የሽብር ቡድኑን የተቀላቀለው ብርሃነ ለሁለት ሳምንታት ወታደራዊ ስልጠና ሲሰጡት ከቆዩ በኋላ ዓላማ ለሌላው ጦርነት ወደ አማራ ክልል እንዳስገቡት መረዳቱን ብርሃነ ያስረዳል።

ይሁንና መተኮስን ሳይሆን መማርን፤ መግደልን ሳይሆን በፍቅር ከቤተሰቦቹ ጋር መኖርን ፍላጎቱ ያደረገው ብርሃነ፤ አመቺ ጊዜ ሲያገኝ እጁን ለመከላከያ ሠራዊት በመስጠት ከአሸባሪው ቡድን በውዴታው መላቀቁን ይገልጻል።

አሁን ላይ የቤተሰቦቹን ሁኔታ ማወቅ ባይችልም እርሱ ግን በመከላከያ ሠራዊት እጅ በመሆኔ የጎደለብኝ ነገር የለም ይላል፡፡

በአግባቡ ተቀብለው ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በተገቢው መንገድ እያስተናገዷቸው መሆኑን ጠቁሞ፤ የትግራይ ወጣቶችም ልክ እንደእርሱ ሁሉ እጃቸውን ለመከላከያ ሠራዊት ቢሰጡ ችግር እንደማይደርስባቸው ማሳያ መሆኑን ብርሃነ ይናገራል።

በትግራይ ክልል ወጣቶች በሌሊት ከቤታቸው እየታፈኑ ለጦርነት እንደሚመለመሉ የሚገልጸው ብርሃነ፤ የአሸባሪው ትሕነግ አመራሮች የትግራይ ሕዝብ ብዙ መከራ ውስጥ ከተውታል እኔንም ከአባቴ ነጥለው ወደጦርነት ማግደውኛል መከላከያ ባያገኝኝ እስካሁን በሕይወት አልቆይም ሲል ነበር ዕድለኛ መሆኑን ተስፋ ባጫረ ስሜቱ የገለጸው።

የሽብር ቡድን አመራር ልጆች በአውሮፓና አሜሪካ የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖሩ የደሃው ትግራይ ሕዝብ ልጆች ግን ወደጦርነት የሚማገዱበት የትግራይ ዲያስፖራ ማኅበረሰብ እንዴት በግልጽ ሊቃወመው እንዳልቻለ ጥያቄን የሚያጭር ጉዳይ ሆኖ ዘልቋል።

የነብርሃነ ታሪክ ግን ልብ ላለው ሃቁን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ዕውነታ ነው። በርካታ ወላጆች በግዴታ ፎርም ልጆቻቸውን ለጦርነት ሲልኩ የአሸባሪው ትሕነግ ልጆችና አክቲቪስቶች ግን በሕዝብ ገንዘብ የተንደላቀቀ ሕይወትን እንደቀጠሉ ነው።

## ከ5 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የንፁሕ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚ መሆናቸውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በ2014 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ አምስት ሚሊዮን 360 ሺህ 290 ዜጎች የንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። በመሆኑም የሀገራዊ የውሃ ሽፋኑን በሶስት ነጥብ 97 በመቶ ጨምሯል።

በበጀት ዓመቱ ሁለት ነጥብ 69 ሚሊዮን በላይ በገጠር የሚኖሩ ዜጎች የንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን የገለፁት ሚኒስትሩ፤ በዚህ ምክንያትም የገጠር የመጠጥ ውሃ ሽፋኑን በሁለት ነጥብ አምስት በመቶ ከፍ ሊል መቻሉን አብራርተዋል።

በተመሳሳይ ከሁለት ነጥብ 66 ሚሊዮን በላይ በከተማ የሚኖር ኅብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ አዲስ የውሃ ተቋማት ተገንብተዋል። ለነባሮቹም ማስፋፊያና ጥገና ተደርጓል። በአጠቃላይም በከተማ እና በገጠር 56 ሺህ 782 የመጠጥ ውኃ ተቋማት በአዲስ መልኩ የመሥራት እና ለነባሮቹ የውሃ ተቋማት ደግሞ ማስፋፊያ እና ጥገና ሥራዎች ተሠርተዋል።

ሆኖም በሀገሪቱ የንፁሕ መጠጥ ውኃ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ይታያል ያሉት ኢንጂነር ዶክተር ሀብታሙ፣ የመጠጥ ውኃ እጥረት በተለይም ለኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች አጀንዳ መሆን እንዳልነበረበት ገልፀዋል።

በዋናነት በተለይ በከተሞች የሚፈጠሩ የንፁሕ መጠጥ ውኃ ችግሮች የውሃ ተቋማቱ ከግንባታቸው ጀምሮ የሚፈጠሩ መሆኑንና ለዚህም መንስዔው የከተሞች የሕዝብ ቁጥር መረጃ መሬት ላይ ካለው ዕውነታ ጋር የማይመጣጠን መሆኑ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የንፁሕ መጠጥ ውሃ እጥረት በሌሎች ችግሮች ምክንያት የሚፈጠር መሆኑንም ነው ያብራሩት።

ለንፁሕ መጠጥ ውኃ እጥረት አንዱ ምክንያት የውሃ ሃብት አጠቃቀም ላይ ያለው ዝቅተኛ ግንዛቤ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሌላ በኩል በኅብረተሰቡ ዘንድ የጠባቂነት



ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ

መንፈስ መኖሩ ሁኔታውን አደገኛ እንደሚያደርገው አብራርተዋል።

ሕዝቡ ውሃን ማግኘት የሚፈልገው መንግሥት ገንብቶ ሲያስረክበው ብቻ መሆኑንና በመንግሥት ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የንፁሕ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶችን በእኔነት ስሜት እየጠበቀ ባለመሆኑ ምክንያት ችግሩን አሳሰቢ ደረጃ ላይ እንዳደረሰው ጠቁመዋል።

ሆኖም ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮችን እየተከተለ መሆኑን ነው የተናገሩት።

በዋናነት ነባርና የኢትዮጵያን አሁናዊ ገፅታ የማይመጥን የውሃና ኢነርጂ አሠራሮችን በመከለስ ብዙ ችግሮች ሊፈቱ እንደሚችሉ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ሌላው የመፍትሔ አማራጭም በኅብረተሰቡ ዘንድ የንፁሕ መጠጥ ውኃ የአቅርቦትና የግንዛቤ ልማድ መቀየር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንደሆነ አብራርተዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ጣቢያዎችን የመንከባከብ፣ የመቆጠብና በኃላፊነት የመጠቀም ግዴታን በማስረፅ ኅብረተሰቡ ውኃና የውሃ ተቋማትን በኃላፊነት መያዝና ማስተዳደር የሚችልበት አግባብ መፍጠር እንደ አንድ መፍትሔ የሚወሰድ ነው። በሌላ በኩል ማኅበረሰቡና የግል ተቋማት በግላቸው ውኃ የሚያለሙበትን አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ሁለተኛው የመፍትሔ አማራጭ መሆኑን አስረድተዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያ ያላትን ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴት ለዓለም በማስተዋወቅ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የበለጠ መሥራት ይገባል››

- የዩኔስኮ ዳይሬክተር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን አስገራሚ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴት ለዓለም በማስተዋወቅ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የበለጠ መሥራት እንደሚገባ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) ዳይሬክተር ዩኒኮ ዩኮዚኪ ተናገሩ።

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም ቅርስነት ካስመዘገበቻቸው የማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ የመስቀል በዓል አንዱ ነው።

በመስቀል ደመራ በዓል ላይ የታደሙት በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) ዳይሬክተር ዩኒኮ ዩኮዚኪ እንደተናገሩት፤ የዓለም ቅርስ የሆነው የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ጠብቆ መቀጠሉን መገንዘባቸውን ገልጸዋል።

የመስቀል ደመራ በዓል እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በ2013 በማይዳሰሱ የአለም ቅርስነት መመዝገቡን አውስተው በኢትዮጵያ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ መሆኑን ጨምረው ጠቅሰዋል።

በመስቀል ደመራ በዓል ላይ የሚቀርቡ ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶች፣ የሕዝቡ አንድነት፣ መተባበርና የአለባበስ ሥርዓት የበዓሉን ይዘት ጠብቀው መቀጠሉን ማሳያ እንደሆነ ጠቅሰው ይዘቱን ጠብቆ ማስቀጠል ተገቢ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የመስቀል በዓልን ጨምሮ ያላትን አስደናቂ ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ዓለም እንዲያውቅ መሥራት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ዩኔስኮ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትን ለዓለም




ዩኒኮ ዩኮዚኪ

ለማስተዋወቅ በአቅም ግንባታና ሌሎች የትብበር መስኮች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር እየሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

በቀጣይም በቱሪዝምና ባህላዊ ቅርሶች ጥበቃ ላይ የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

የተለያዩ የዓለም ሀገራት ጎብኝዎች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የመስቀል በዓልን አስገራሚና ደማቅ ትዕይንቶች እንዲካፈሉ ዳይሬክተሯ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች አስገራሚ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ያላት ሀገር በመሆኗ የማስተዋወቅና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራ መጠናከር እንዳለበትም አስገንዝበዋል።



## “ሀገር በተደፈረች ጊዜ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቢያደርግም ከቆይታ በኋላ ሕይወቱ አልፏል።

በጎንደር የተወለደው ድምጻዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ለሙዚቃ ካለው ፍቅር የተነሳ በተወለደበት አቅራቢያ የሚገኝ የወታደር ካምፕ በመግባት በካምፑ በሚገኝ ኦርኬስትራ ውስጥ ሙዚቃ መጫወት እንደጀመረ ይታወሳል።

በማዲንጎ ድምጽ የተገረሙት ወታደሮችም “ማዲንጎ” የሚል ስያሜ ያወጡለት ሲሆን ሕይወቱ እስካለፈበት ጊዜ በዚሁ ስም ሲጠራ ቆይቷል።

በ10 ዓመቱ ወደ አዲስ አበባ “ዜማ ላስታስ” ባንድ በመግባት የሙዚቃ ሕይወቱን ቀጥሏል።

ድምጻዊ ማዲንጎ “ስያሜ አጣሁላት”፣ “አማን ነው ወይ ጎራው” እና “ትዝታ” በሚባሉት ዘፈኖቹ ይታወቃል።

ድምጻዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ዘመን የሚሻገር ሥራዎችን አከናውኗል።

ኢትዮጵያ በተፈተነችበት ወቅትም እያመመው ግንባር ድረስ በመሄድና የውትድርና ማሰልጠኛዎች ድረስ በመሄድ ምልምል የሠራዊት አባላትን በሥራው በማነቃቃት የራሱ የሆነ ታሪክ የሠራ አርቲስት ነው።

# አሸባሪው ትሕነግ እንደሚጠፋ በመገንዘቡ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሸባሪው ትሕነግ ወደ ጦርነት እየገባ ያለው በመንገዱ ያገኘውን ሕዝብ እያፈሰ ነው፤ ይህ ደግሞ ሆን ብሎ የሽብር ቡድኑ ለመጥፋት ቅርብ ስለሆነ ሕዝቡንም ይዞ ለመጥፋት ካለው ፍላጎት ነው ብለዋል፡፡

አሸባሪው ትሕነግ ሕጻናትንና ሽማግሌዎችን ያለምንም ኅዘኔታ ወደ ጦርነት እንዲወጡ ማድረጉ የቡድኑ የመጥፊያ ጊዜ እንደቀረበ የሚያመላክት ነው ብለዋል፡፡

የሕወሓት ኃይል ሕዝብ ላይ ነው ያለው፤ በሕዝብ ስም ነው የተከለሉት ለዚህም ነው ሕዝብን በማገት እና በማፈን ወደ ጦርነት እያስገቡ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከገባበት ችግር ለመውጣትና ከአሸባሪው ትሕነግ አገዛዝ ለመላቀቅ ኢጋዥ ይፈልጋል ያሉት አቶ ብርሃነ፤ ሕዝቡ በትሕነግ የሽብር ቡድን ስር በመሆኑ አማራጭ በማጣቱ አሸባሪው ኃይል እየተጠቀመበት ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት ኃይሉን በማጠናከርና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ሕዝብ ሳያልቅ በፍጥነት የትሕነግ የሽብር ቡድን ሕግ ፊት እንዲቀርብ የሚችልበትን መንገድ መከተል አለበት ብለዋል፡፡ በቡድኑ ምክንያት የትግራይ ሕዝብ በጦርነት ብቻ ሳይሆን በረሃብ ጭምር እንዲሰቃይ የሽብር ቡድኑ እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ጥቂቶቹ የሽብር ቡድኑ መሪዎችን በመያዝና ወደ ሕግ በማቅረብ የትግራይ ሕዝብ ነጻ ማውጣት ከመንግሥት ይጠበቃል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ብርሃነ ገለጻ፤ በትሕነግ አስገዳጅነት ወደ ጦርነት የገባ የትግራይ ወጣት ወደ ትሕዴን በመምጣት ሕይወቱን እያዳነ ይገኛል፡፡ አሁንም የትግራይ ወጣት ከሽብር ቡድኑ ትሕነግ ተላቆ ወደ ትሕዴን በመቀላቀል ሕይወቱን ሊያተርፍ ይገባል ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ‹‹ኢትዮጵያ የገጠማትን ፈተናዎች በድል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያለንን አክብሮትና ደጀንነት ለማረጋገጥ ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከገጠሟት ፈተናዎች በድል እንድትወጣ ከተማ አስተዳደሩ ለመከላከያ ሠራዊት የሚያደርገውን ሁለንተናዊ የደጀንነት ሚና አጠናክሮ እንደሚቀጥልም በዚህ ወቅት አረጋግጠዋል።

የከተማ አስተዳደሩ የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ-ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ጀማሉ ጀንበር በበኩላቸው፤ አሸባሪው ትሕነግ ከውጭ ግብረ አበሮቹ ጋር በማበር የከፈተው ጦርነት በጀግናው መከላከያ ሠራዊት እየተመከተ ይገኛል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት አጋርነቱን ለማሳየት ከበጎ ፈቃደኛ ተቋማትና ግለሰቦች ድጋፍ በማሰባሰብ በመስቀል በዓል ማዕድ በማጋራቱ ክብር ይሰማዋል፤ ድጋፉንም አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የጦር ኃይሎች አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዋና አዛዥ ብርጋዴር ጄነራል ዶክተር ኃይሉ እንዳሻው በበኩላቸው ሕዝብና መንግሥት ለመከላከያ ሠራዊት እያደረጉ ያለው ሁለንተናዊ ድጋፍ ለሠራዊቱ ትልቅ የሞራል ስንቅ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዕለቱ ለተደረገው የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብርም አመስግነዋል።

ጀግናው የአገር መከላከያ ሠራዊት በግንባር ከሚፈጽመው ጀብድ ባሻገር የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስና ሰብል በማጨድ ሕዝባዊ ሠራዊት መሆኑን ያረጋገጠ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የወያኔ ሴራ ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ግብዓተ መሬቱ እስኪፈፀም ድረስ የሚደረገው የደጀንነት ሚና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

# የሽብር ቡድኑን ወደስልጣን ለመመለስ የሚጥሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጥቅም የሚያስቀድሙትና የሚቆሙለት ዓላማ እንደሌለ ያሳያል ብለዋል፡፡

በመሆኑም አሸባሪው ትሕነግ ከውጭ ኃይል ሚዲያዎች የፕሮፖጋንዳ ድጋፍ ያገኛል ያሉት አቶ ዓለሙ፤ የሽብር ቡድኑ የሚያካሂደው ጦርነት የተለየ ባሕሪው በፕሮፖጋንዳ ሥራ መታገዝ መቻሉ እና የፕሮፖጋንዳ ሥራውም በውጭ ኃይሎች ድጋፍ የሚሰጠው መሆኑ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

እነዚህ የውጭ ኃይሎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር በሚያደርጉት ጥረትም አሸባሪው ትሕነግ የጦርነት ትንኮሳ አካሂዶ እራሱ እንደተጠቃ አድርጎ በሚገልጽበት ጊዜ ይህን ተከትለው ፕሮፖጋንዳውን የሚያቀባብሉት የእነሱ ሚዲያዎች እንደሆኑ ነው የጠቆሙት፡፡

እንደ አቶ ዓለሙ ገለጻ፤ የውጭ ኃይሎች ሚዲያዎች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እና ብዙ ሽፋን ያላቸው በመሆኑ በቀላሉ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተደራሽ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የጦርነት ትንኮሳውን የጀመረውን ቡድን ሳያጠኑና ሳይመረምሩ አሸባሪው ትሕነግ የሰጣቸውን መረጃ ተቀብለው ዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ዘገባ ይሠራሉ፡፡ በዚህም ዓለምን በማሳሳት ኢትዮጵያ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡

አሸባሪው ትህነግ በዜጎች ላይ ያስከተለውን ሰብዓዊ፣ ቁሳዊ እና ኢኮኖሚያዊ ውድመት በማጥናት መሳተፋቸውን የገለጹት የሕግ ትምህርት ክፍሉ ዲኑ፤ ቡድኑ በተለይ ሴቶች ላይ በዓለም ላይ ታይቶ የማይታወቅና ከግብረ ገብነት አንፃርም የማይገመት ግፎችን ሠርቷል ብለዋል፡፡

አሸባሪው ትሕነግ አባት ልጁን እንዲደፍር የማድረግ፣ አስገድዶ ተመሳሳይ ፆታ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ የማስደረግ ፣ ሴቶችን ደፍሮ በኤች.አይ.ቪ ኤድስ የማስያዝና የመሳሰሉትን ግፎች መሥራቱን በጥናቱ ወቅት መመልከታቸውን ተናግረዋል፡፡

ይህ ሁሉ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚከለክለው ቢሆንም በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች እንዳይተላለፍ ሆኖ የቀረው በእነዚሁ የውጭ ኃይሎች ሴራ ነው ሲሉም ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም በነዚህ የውጭ ሚዲያዎች የሐሰት ዘመቻ ላይ በኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ በሕዝቡ በኩል ችግሩን የሚፈቱ እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደሚገባ አቶ ዓለሙ ይገልፃሉ፡፡

በኢትዮጵያ በኩልም የነዚህ ሚዲያዎችን የሐሰት ዘመቻ የሚያከሽፍ እና ዕውነት የሚያወጣ ዓለም አቀፍ ሚዲያ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ይመክራሉ፡፡

እንደ አቶ ዓለሙ ገለጻ፤ በአንድ ጀምበር ሚዲያዎችን ዓለም አቀፍ ማድረግ አይቻልም፤ ሆኖም ተቀባይነት ያላቸው በተመሳሳይ ደረጃ ሊታዩ የሚችሉ ሚዲያዎችን ከአሁኑ ጊዜ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በኩል ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች መፍጠር እስኪቻልም የምዕራባውያን ተቀናቃኝ የሆኑ ዓለም አቀፍ ተሰሚነት ያላቸውን ሚዲያዎች መጠቀም እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ተደማጭነታቸው በተመሳሳይ ደረጃ ያሉ ሚዲያዎችን ለአብነትም አር.ቲ እና ሲ.ጂ.ቲ.ኤን የመሳሰሉ ገለልተኛ ሚዲያዎችን እንደአማራጭ በመጠቀም ዕውነታዎችን ማጋለጥ ይገባል ብለዋል፡፡

በሕዝቡ በኩልም ማኅበራዊ ሚዲያዎችን ለዚህ ዓይነት ትግሎች መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን አክለዋል፡፡

በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲዎች በክስተቶቹ ዙሪያ ጥናትና ምርምሮችን እንዲሠሩ ማበረታታትና ለዓለም አቀፉ ተቋማት ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ የውጭ ኃይሎችን ሚዲያዎች የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ለማጋለጥ የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፈተናዎቻችን ከጥንካሬያችን ለመነጩት ብዙ ስኬቶቻችን መሠረት ሆነውናል!

ያለፈው ዓመት እንደ ሀገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ያለፍንበት ፣ ከፈተናዎቹ ጥንካሬ የተነሳም አንዳንዶች አበቃላቸው በሚል ሟርት የዓለም አደባባዮችን ሳይቀር ያደመቁበት ፤ከዚህ በመነጨም ከፍ ባለ ድምጽ ፌሽታ ሲያሰሙ የተስተዋለበት ዓመት ነበር ። ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ሟርቱን እውን ለማድረግ አጋጣሚዎችን ሁሉ ለመጠቀም የዳከሩበት ጭምር ነበር።

በአንድ በኩል የናት ጡት ነካሽ የሆነው አሸባሪው ትሕነግ በእብሪት ያጣውን ስልጣን በኃይል ለመመለስ በለኮሳቸው ሶስት ዙር የእብሪት ጦርነቶች በአማራና በአፋር ሕዝቦች ላይ ከፍ ያሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችንና ሰብዓዊ ቀውሶችን ፈጥሯል። የትግራይንም ሕዝብ ከፍ ላሉ ሰብዓዊ ቀውሶች ዳርጓል።

በሌላ በኩል ለውጡና የለውጡ ኃይል ይዞት የተነሳው የፖለቲካ አስተሳሰብና አስተሳሰቡ የፈጠረው ሀገራዊ መነቃቃት ያላስደሰታቸው ኃይሎች ለውጡን ከጅምሩ ለመቀልበስ አሸባሪውን ትህነግ ጨምሮ ሌሎች አሸባሪ እና ጽንፈኛ ቡድኖችን በመጠቀም ረጅም ርቀት ሄደዋል። ዓለም አቀፍ ተቋማትን ለዚሁ ዓላማቸው መጠቀሚያ በማድረግም ሀገርና ሕዝብን በብዙ ተፈታትነዋል ።

በታሪኩ ባልተለመደ ሁኔታ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት /ተመድ / የጸጥታው ምክር ቤት ከ12 ጊዜ በላይ ኢትዮጵያን የመነጋገሪያ አጀንዳ አድርጎ ታይቷል። በዚህም በሀገሪቱ ላይ ጫናዎችን ለማድረግ ሰፊ ጥረት ተደርጓል።ጥረቱ ፍትህ ወዳድ በሆኑ ሀገራት የታሰበውን ያህል ውጤታማ ባይሆንም ክስተቱ ግን ታሪካዊ ሆኖ አልፏል።

በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም መንግሥት ላይ ጫና ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች ፤ ከሁሉም በላይ አሸባሪው ትሕነግ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ጉዳዮች ያለመከሰስ መብት ያለው ያስመሰለ ፤ቡድኑ መብቶችን በመጣስ እየሄደበት ባለው የጥፋት መንገድ እንዲገፋበት የልብ ልብ ሆኖም የታየ ነበር።

ይህ በሀገር ውስጥ አሸባሪና ጽንፈኛ ቡድኖች በታሪካዊ ጠላቶቻችንና የለውጡ አካሄድ ባሰማራቸው ኃይሎች ጥምረት በብዙ የተፈተንበት 2014 ዓ.ም ብዙ ዋጋ ቢያስከፍለንም በወቅቱ እንደ ሀገር ዋነኛ ተግዳሮት የነበረውን የሀገረ መንግሥቱን ሕልውና በጠንካራ መሠረት ላይ በማዋቀር አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጅማሬያችንን በማብሰር ተጠናቋል ።

የትናንት ፈተናዎቻችን ጠላቶቻችን በአደባባይ እንዳሟረቱት ሳይሆን ፤እንደ ሀገር ጠንክረን እንድንወጣ አድርገውናል፤ የትናንት ፈተናዎቻችን ዛሬ ላይ በትናንት አቅማቸው የማይፈትኑን ደረጃ ላይ አድርሰውናል፤ በቀደሙት ፈተናዎቻችን መጋፈጥና ማሸነፍ የሚያስችል አቅም አጎናጽፈውናል። በፈተናዎች ውስጥ ጥንካሬ፤ በጥንካሬ ውስጥ ተስፋ እና ድል መኖሩን አስተምረውናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የመስቀል በዓልን በማስመልከት ባስተላለፉት መልዕክታቸው “በአስቸጋሪና በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈን እዚህ ደርሰናል። መንገዳችን ጨለማ፣ እግራችን ቁጤማ እንዲሆን ብዙ ተሠርቶብናል። ከድጡ ወደ ማጡ እንድንወርድ ያልተፈተለ ሤራ የለም። እንጀራችንን የበሉ ተረከዛቸውን አንሥተውብናል። ወንዙ እንዲሞላብን፣ ጎርፉ እንዲደርስብን፣ ናዳ እንዲወርድብን ብዙ ተሠርቶ ነበር።

“ስለ ረሃብ እየተነገረብን፣ ምድሪቱ አትረፍርፋ ሰጠችን። ስለ በረሃማነት እየተሟረተብን ሀገራችን አረንጓዴ ለበሰች። ስለ ኪሣራ እየተለፈለፈ፣ ኢኮኖሚያችን ፈተናዎቹን እየተሻገረ ቀጠለ። ከግራ ከቀኝ እየተዋከብን ሦስተኛውን ዙር የሕዳሴ ግድብ ሞልተን ተርባይናችንን አስነሣን። እንድንለያይ መዓት እየተወራ፣ የሕዝባችን አንድነት እንደ ብረት ጠነከረ፤ እንደ አልማዝ አበራ። ደክመዋል ተብሎ ሲዘመትብን፣ በጽናት ቆመን አሳየን። የትም አያደርሷቸውም የተባልንባቸው ፕሮጀክቶቻችን በመጠናቀቅ ላይ ናቸው“ ማለታቸው ለዚህ ነው ።

በርግጥም ፈተናዎቻችን ለዛሬው ጥንካሬያችን ፤ ከጥንካሬያችን ለመነጨው ብዙ ስኬታችን መሠረት ሆኖናል። ወደፊትም ጠላቶቻችን የሚፈጥሩልን ፈተናዎች የበለጠ እያጠነከሩን የጀመርነው የለውጥ ጉዞ ለስኬት የሚያበቁ የአቅም ምንጮቻችን ሆነው ያገለግሉናል። በዚህም በታሪክ በለውለታዎቻችን ሆነው ይታወሳሉ!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የተመድ ሰብአዊ መብት «ሪፖርት» እና የ«ካፈርኩ አይመልሰኝ» አቋሙ

ግርማ መንግሥቴ

ጉዳዩ አዲስ ሳይሆን የተለመደ ነው። አንድ ነገር ሲለመድ ባህርይ ይሆናል እንደሚባለው ነውና ስራቸው የባህርይ በመሆኑ የማንም ሆድ አልተረበሸም። ይልቁንም “ትዝብት ነው ትርፉ ...”ን አዜመ እንጂ፤ “ጉዴ ነው” ሲል የቆዘመ አንድም የለም።

አነሳሳችን በሰሞኑ ጉድ ላይ አንዳንድ ሃሳብ ለመለዋወጥ ነው። ይህ የሰሞኑ ጉድ ደግሞ “በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈፅሟል የሚል ከሕወሓት ጋር እየተደረገ ባለው ጦርነት የኢትዮጵያ መንግሥት “ተጠያቂ” የሚያደርገውና የተሰራጨው “ሰነድ” ሲሆን፤ ሪፖርቱን/ክሱን እንደ ብዙዎቹ “መሰረተ ቢስ” ብሎ ከማለፍ በዘለለ አንዳንድ ጉድፎቹን ለማሳየት ነው።

ሪፖርቱ “የተለመደ ነው” ስንል ያው ምንም አዲስ ነገር የለውም፤ ባጭሩ ”Cooked data” የሚሉት የተጋገረ መረጃ ነው። ይህ የተለመደ አውሮፓዊ ምስርት የሆኑ ተቋማት መረጃ የመጋገር አባዜ፣ ልምድ፣ አላማና ርእዮተ አለም (ካስፈለገ “ኒዎሊበራል ቶውት” በሉት) አዲስ ሳይሆን፤ አሮጌ ካቲካላ በአዲስ ጠርሙስ ነው። የስካሩ ከፍታም መነሻው ይሄው ሲሆን፤ በተለይ ጋገራው አፍሪካ ላይ ማተኮሩና ተጣብቆ፣ አልላቀቅ ብሎ ያለውም እዚሁ የፈረደባት “ማዘር አፍሪካ” ላይ መሆኑ ነው።

ማንም እንደሚያውቀው፣ ገብተው እንደ ፈለጉ የመሆንና እጅ የመጠምዘዝ አካሄድ ፍልስፍና (Neoliber-alism)ን በአፍሪካ ላይ ለመጫን የማይፈልግ የለም። ይህ “አፍሪካን እንደገና ለመቀራመት” (የ1884ቱን የበርሊን ኮንፈርንስን ያስታውሷል) እየተደረጉ ካሉት “ዘመናዊ” ጥረቶች አንዱ አካል የሆነው የመረጃ ጋገራ ተግባር ሰበቡ ኢትዮጵያ ትሁን እንጂ ሾተሉ ያነጣጠረው ጠቅላላ አፍሪካ ላይ ስለመሆኑ የአሜሪካ ባለስልጣናትን ከውሃ ቀጂ በፈጠነ ምልልስ አፍሪካን እያጨናነቋት የመሆናቸው ጉዳይ ነው።

ከመቆጣት፣ ማስፈራራት ... አልፎ፣ ዛሬ ወደ ግልፅ የውክልና ጦርነት የገባው የ“ኒዎሊበራል ቶውት” አራማጅ ኃይል ህልሙ እየከሸፈ መሆኑ እየገባው ሲሆን፣ በካፈርኩ አይመልሰኝ አቋሙ በመፅናት፣ በኢትዮጵያ መነሻነት አፍሪካን እንደገና ሊያስገብር እየተጋጋጠ ይገኛል።

ሪፖርቱን በተመለከተ አስቀድመው (ሰሞኑን) ባለ ሪፖርቱ በሚገባው ቋንቋ እስኪበቃው የነገሩት አካላት ስላሉ ይህ ጽሑፍ አንቀፅና ገጽ እየጠቀሰ ድክመትና ሀጢያቱን አይን ከሰበከት እያገላበጠ ማሳየት ላይ አያተኩርም።

የዚህ ጽሑፍ ዐቢይ ትኩረት የሪፖርቱ “ስለምን?” ላይ ነውና በእሱው ላይ ሀሳብ ይሰነዝራል። ከዛ በፊት ግን፣ በጥቅሉ ማለት ነው፣ ሪፖርቱ በበቂ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ፣ ተገቢውን ናሙና ከተገቢ ቦታዎች (ምንጮች) ያላካተተ፣ የይድረስ ይድረስና ለአንድ ለታቀደ አላማ ቶሎ እንዲደርስ ታስቦ ለአየር የበቃ፣ ሲበዛ አድሏዊ፣ እጅግ ሲበዛም ወገናዊ (ወጋኝ)ነው።

አብዛቶም አለም ከሚከተለው ተገቢና ትክክለኛ የጥናትና ምርምር መርህ የተጣላነው ፤... ሲሆን፣ ባጭሩ ከዚህ በፊት አንዴ ተነክሬበታለሁና ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ድንቁርና ላይ የተመሰረተና እጅጉን ስነምግባር የጎደለው መሆኑ በተለያዩ አካላት በአንድ ድምፅ መነገሩን ጠቆም አድርጎ ማለፉ ተገቢ ነውና እናድርገው።

የወዲያ ማዶ ሰዎችን፣ የ#NoMore ንቅናቄ ወደ #No-More_Colonialism መሸጋገሩ ጭራሽ እያሳበዳቸው እንጂ እንዲሰክኑና የእስከ ዛሬውን ስህተታቸውን ገምግመው፣ አርመው ... የወደፊቱን እንዲያቃኑ ሊያደርጋቸው አልቻለም። በቱርጁማን አማካኝነት፣ በአማርኛም “አፍሪካን ዳግም ለመቀራመት አይቻልም” ቢባሉም ጆሯቸው ከመስማት ውጪ ሊያዳምጥ አልቻለም፤ ወይም፣ አልፈለገም።

ከ50 በላይ የሆኑ አፍሪካዊ ያልሆኑ ሀገራት አፍሪካን (ምንም እንኳን ኢትዮጵያን ባይመለከትም) ለዘመናት በቅኝ ገዥነት ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የነበሩበትን ዘመን ዳግም ለማስቀጠል ከመቋመጥ የዘለለ እቅድም ሆነ ራእይ የሌላቸው በመሆኑ፤ አፍሪካ ወደ ምስራቁ ጎራ ዞር ልትል ነው፤ በመሆኑም ከመዞሯ በፊት ባለ በሌለ ኃይላችን የመዞሯን ጉዳይ ከወዲሁ ልናጨልመው ይገባል በሚል ዘመኑን ያልመጠነ አስተሳሰብ እየተመሩ፤ ያንንም ለማሳካት እያጫረሱን ይገኛሉ። እኛም ደካማ ጎናችንን መድፈን አቅቶን እየተጫረስንላቸው እንገኛለን። በመሆኑም እያደረጉት ያሉት ተግባር ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ንቀትም ጭምር ነው።

በአንድ ወር ውስጥ ከ12 ጊዜ በላይ በኢትዮጵያ ላይ በተሰበሰቡበት ጊዜ “ይህ አይን ያወጣ የቅኝ ገዥዎች ሴራ አንድም አፍሪካዊ ሀገር በማይገኝበት፣ በሌለበት በኢትዮጵያ ጉዳይ ለመነጋገር የጠሩት ልዩ ስብሰባ አለም አቀፍ ሕግን የሚጻረር፣ ለአፍሪካ ሕዝብ ያላቸውን ከፍተኛና ገደብ የለሽ ንቀት የሚያሳይ፣ ዛሬም የቅኝ ገዢነት ፍላጎታቸውን ለማሳካት የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለመመዝበር፣ ለመቀራመት፣ በማያገባቸው እየገቡ ለእነሱ ተላላኪና አሽከር የሆነ አሻንጉሊት መንግስት ለመመስረት የሚያደርጉት ሴራ ስለሆነ አፍሪካውያንም፣ መላው የአለም ሕዝብም ያወግዙታል።

“የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ G7 ሀገራት፣ የአውሮፓ ሕብረት አፍሪካን አይወክሉም። የቅኝ ገዢዎችና የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች ስብስብ ነው። አፍሪካ ራሷን ከእነዚህ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ማግለል ይጠበቅባታል” ተብሎ ተጽፎ ቢነገራቸውም ንክች ያባ ቢላዎ ልጅ ብለው እነሆ በአንዲት ሉአላዊት አገር ላይ በሀሰት ሪፖርት ላይ የሀሰት ሪፖርት፤ በግፍ ላይ ግፍ ... እየደራረቡ ይገኛሉ።

የቀድሞው መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም “ደፍረውናል፣ ንቀውናል፣ ብታምኑም ባታምኑም ...” ያሉት ነገር እየተደጋገመ በብዙዎች ሲነሳላቸው ይሰማል፤ እውነት ነው። አባባሉ ዛሬም ቦታ አለውና እኛም እንደግመዋለን።

አሜሪካ የራሷ ሀገር ሕዝብ በነጮች ዘረኝነትና በዴሞክራሲ እጦት እየተሰቃየ ለሌላው አለም ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት፣ ፕሬስ ነጻነት እቆማለሁ ... የምትለን ’ስለ እኔ ምንም አያውቁም’ ከሚል ንቀት የመጣ እንጂ ሌላ አይደለም። ካናዳ ውስጥ የተፈፀመውንና የተገኘውን የጅምላ መቃብር እንዳላየ የሚያልፍ የዩኤን ሰብአዊ መብት ዘርፍ፤ ቡድኑ ማይካድራ ላይ የሰራውን ዘግናኝ ስራ ባላየ የሚያልፍ ተቋምን ... ኢትዮጵያ ላይ ሲሆን የሌለ ሁሉ የሚታየው ከድፍረትና ተመፅዋችነታችን (ፊታችንን ወደ ልማት እናዙር የሚባለው ከዚህ ለመውጣት ነበር) የመጣ እንጂ ከሌላ ከምንም ሊሆን አይችልም።

አፍሪካዊ ሉአላዊነታችንን በመጋፋት “አፍሪካ ከቻይናና ሩሲያ ጋር ገጠመች” በማለት ግራ ኋላ ሊያዞሩን የሚፈልጉት አፍሪካውያን አልሰለጠኑም ከሚለው የልጅነት አስተሳሰባቸው ካለመውጣት ቢሆንም፤ እኛን የጉሎ ዘይት ለማጠጣት የታቀደ አይደለም ማለት አይቻልምና ዛሬ አፍሪካ አንድ ሆና ልትቆም የግድ ይሆናል።

በተለያዩ ምድር አንቀጥቅጥ ሰልፎች፣ እዛው አሜሪካ እና አውሮፓ ምድር ላይ “አፍሪካ የአሜሪካ ሞግዚትነት አያስፈልጋትም፤ ኢትዮጵያ ነጻና ሉአላዊ ሀገር እንደመሆኗ መጠን የማንንም ጣልቃ ገብነት አትቀበልም፤ የአውሮፓ ሕብረት በኢትዮጵያ ጉዳይ የጠራው ስብሰባ ሕገወጥና ተቀባይነት የሌለው ነው ...” ወዘተርፈ ተብሎ ቢነገርም የሚመለከታቸው ጆሮ ሊሰማ፤ አይናቸውም ሊያይ - በአጠቃላይ አምስቱም የስሜት ህዋሳቶቻቸው በድን ከመሆን ውጪ ሊሰማቸውና ወደ መሀል ሊመጡ አልቻሉም።

ይህ ደግሞ ካፈርኩ አይመልሰኝ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም፣ የአሁኑ ሕወሓትን ሆኖ፣ ለእሱም ከእሱ ከራሱ በላይ ወግኖ ...፤ ሰብአዊ መብት የሚል ታግ ለጥፎ፤ ከአቀራረብ እስከ ይዘቱ ድረስ የተጋገረን ጥናት “እነሆ ሪፖርት” ማለቱ ለማንም አይበጅምና፤ ከአፍሪካ ጋር አብሮ ለማደግና እኩል ተጠቃሚ ለመሆን ሳይረፍድ ወደ መስመር መግባት ያስፈልጋል። ቻው።

# ፍረዱኝ

# በመማርና ማስተማር አጣብቂኝ ውስጥ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ፍሬ ነገሩ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 በሚገኙት ህጻን ዓለም አፀደ ህጻናት እና አምስት ኪሎ አፀደ ህጻናት በሚያስተምሩ በመምህራን እና የሽማች ህብረት ሥራ ማህበር መካከል የተፈጠረ አለመግባባትም የሚመለከት ነው። ይህን ጉዳይ ከሁለት ወር በፊት «ወደ መጠጥ ቤት የተቀየረው ትምህርት ቤት ውዝግብ» በሚል ርዕስ ለአንባቢያን ማቅረባችን ይታወሳል። ታዲያ ከዚህ ዘገባ በኋላ ምን አዲስ ነገር አለ? ስንል ወደ ክፍለ ከተማው እና ወረዳው በማቅናት የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች በማናገር ተከታዩን መረጃ አጠናቅረናል።

**ቅሬታ አቅራቢ መምህራን**

በወቅቱ በደል ተፈጽሞብናል ሲሉ አቤቱታ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኙት ህፃን ዓለም አጸደ ህጻናት እና አምስት ኪሎ አፀደ ህጻናት መምህራን ነበሩ። «በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኘው የሽማቾች ህብረት ስራ ማህበር በ2004 ዓ.ም በአደራ ከተረከባቸው ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነውን ህጻን አለም አፀደ ህጻናት ማስተማሪያ ህንጻ ወደ መጠጥ ቤት በመቀየር ተማሪዎችን ከመበተኑ ባለፈ መምህራንንም ላልተጋባ እንግልት ዳርጓል።

በወቅቱ ሸማች ማህበር በአደራ የተረከበውን የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት የሚያስተምሩ መምህራንን ጥቅማ ጥቅም በመከልከል እና መምህራንን አሰላችቶ ትምህርት ቤቱን ለቀው እንዲሄዱ በማድረግ የትምህርት ቤቱን ህንጻ ለግል ጥቅም ለማዋል በማሰብ በደል እየፈጸሙብን ነው» ሲሉ ነበር። ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ቅሬታቸውን ያስረዱት፡

ከአቤቱታ አቅራቢዎች መካከል መምህርት ዓለም ጌታቸው አንዷ ነበሩ። በህጻን ዓለም ትምህርት ቤት መምህርት ናቸው። በትምህርት ቤቱ ለ30 ዓመታት ያህል መሥራታቸውም ይታወቃል።

ከ2004 ዓ.ም በፊት ህጻን ዓለም ትምህርት ቤት የህዝብ ትምህርት ቤት እንደነበርና በ2004 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ እና ህዝብ ያስተዳድራቸው የነበሩ ትምህርት ቤቶች በመንግስት አስተዳደር ሥር እንዲሆኑ ተወሰነ። ይህን ተከትሎ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ይገኙ የነበሩ በርካታ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መንግስት እንዲያስተዳድራቸው ሆነ ይላሉ መምህርት- ዓለም ጌታቸው።

ይሁን እንጂ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ከሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል ህጻን አለም አጸደ ህጻናት እና የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ምክንያቱ ባልተወቀ አግባብ ለሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር በአደራነት ተሰጡ። ትምህርት ቤቶች ለማስተዳደር በአደራ የተቀበሉት አካላት ስለሙያው ግንዛቤ የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እያደር የትምህርት ቤቱ ህልውና ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ መጣ። መምህራኑ በትምህርት ቤቱ መምህራን እና ህጻናት የሚፈጸሙ ሁሉም አስተዳደራዊ በደሎች ከነገ ዛሬ ይሻሻላሉ በማለት በተስፋ በመስራት ላይ ሆነው የወረዳ 6 የሸማች ማህበር የህጻን አለምን አጸደ ህጻናትን ህንጻ ለማደስ በሚል ሰበብ መምህራን ሙሉ ተማሪዎቻቸውን ይዘው ወደ አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት እንዲቀላቀሉ መደረጉንም ይናገራሉ።

ወደ አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ተደርበው እንዲሄዱ ሲደረግ የትምህርት ቤቱ ህንጻ የቤቱ እድሳት እስከሚያልቅ ተብለው እንደነበር የሚናገሩት ቅሬታ አቅራቢዋ፤ ይሁን እንጂ የህንጻው እድሳት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ነበሩበት ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እንዲመለሱ ሸማቾችን ቢጠይቁም ለዓመታት ትውልድን ሲቀርፁበት የነበረው ትምህርት ቤት «ለመጠጥ ቤት አገልግሎት መዋሉን» እንደተነገራቸው ያስረዳሉ።


አቶ ጀማል እስማኤል

እንደ አቤቱታ አቅራቢዋ ገለጻ ፤ እስካሁን ድረስ ደመወዝ የሚከፈላቸው በህጻን ዓለም ትምህርት ቤት ሥም ነው። ለመከላከያ እና መሰል ሀገራዊ ግዳጆች መዋጮ የሚያደርጉትም በህጻን አለም አጸደ ህጻናት ስም ነው። በህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት ሆነ በአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት ሲሰሩ የሚከፈላቸው ደመወዝ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚሰሩ መምህራን እጅጉን ያነሰ ነው፤ የሚሉት አቤቱታ አቅራቢዋ፤ የመምህራን ጥቅማ ጥቅም የሚባል ነገር ፈጽሞ እንደማይታሰብ ያስረዳሉ።

እንደ መንግስት መምህራን የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው እና ጥቅማ ጥቅሞችም እንደከበሩላቸው በተደጋጋሚ መጠየቀቻውን የሚናገሩት መምህርቷ ፤ እናንተ አክሳሪ እንጂ አትራፊ ስላልሆናችሁ ደመወዝ አይጨምርላችሁም የሚል መልስ ከሸማቾች እንደሚሰጣቸው መናገራቸውንም የዝግጅት ክፍላችን ዘግቦት ነበር።

አቤቱታ አቅራቢዎቹ እንደሚናገሩት፤ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩና በአቻ ደረጃ የሚገኙ መምህራን የቤት አበል እስከ 3ሺብር ፤ የትራንስፖርት ( ፐብሊክ ሰርቪስ እና አንበሳ አውቶቡስ) እንዲሁም ደመወዛቸው ደግሞ ከ10 ሺህ ብር በላይ ሲሆን የእርሳቸው ግን 30 ዓመታትን በማስተማር አሳልፈው በወር ያልተጣራ ሦስት ሺህ ብር ብቻ እንደሚከፈላቸው ይናገራሉ።

ይህም የኑሮ ውድነቱን ያላገናዘበ ከመሆኑም ባሻገር ሞራል የሚነካ ድርጊት መሆኑን ያስረዳሉ። «ስለሆነም በእኛ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ መንግስት እና የኢትዮጵያ ህዝብ ይመልከትልን» ሲሉ ተናግረው ነበር።

**ለመምህራን ቅሬታ የተሰጠው ምላሽ**

ታዲያ ይህ ቅሬታ ለዓመታት ሲንከባለል የነበረ ቢሆንም መፍትሄ ለመስጠት በቂ ጥረት አለመደረጉን የሚናገሩ አሉ። ሆኖም በቅርቡ የሥራ ኃላፊዎች በአሁኑ ወቅት ያለውን የኑሮ ውድነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ጭማሪ መደረጉን ይናገራሉ። በዚህም መሰረት ለመምህራኑ በአማካይ ከ200 ብር እስከ 1000 ብር ጭማሪ ተደርጓል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 06 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አበራ አጌና እንደሚሉት፤ መምህራን በተከታታይ ሲያቀርቧቸው በነበረው ቅሬታ ላይ መጠነኛ ምላሽ ያገኙ ቢሆንም አሁንም ጥያቄያቸው ሙሉ ለሙሉ አለመመለሱን ያብራራሉ።

መምህራን የደመወዝ ጭማሪ ቢደረግላቸውም አሁን ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አይደለም በሚል ቅሬታ እንዳላቸው ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ትምህርት ቤቱን ወደ ቀድሞ ስራው በአግባቡ ለመመለስና አስተዳደራዊ ጉዳዮችንም በአግባቡ ለመምራት የሚችል አመራር የለም የሚለው የመምህራን ቅሬታ አሁንም አለ።

በተለይም በሸማቾች መተዳደሩ የመምህርነት ሙያን ከአገልግሎት አኳያ ሳይሆን በሌላ የንግድ ዕይታ እንዲዳኝ የተዛባ እይታን እየፈጠረ ነው የሚለው ቅሬታ አሁንም መኖሩን ያብራራሉ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የህብረት ሥራ ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጀማል እስማኤል በበኩላቸው፤ ትምህርት ቤቱን ሆነ መምህራን በተመለከተ አሁንም ቢሆን ያልተፈቱ ጉዳዮች ቢኖሩም የተወሰነ የመፍትሄ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውን ይገልፃሉ። የኑሮ ውድነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት የደመወዝ ጭማሪ የተደረገ ሲሆን፤ በሂደት የሚስተካከሉ ጉዳዮች እንደሚኖሩም ይናገራሉ።

በሌላ ጎኑ ግን በሸማቾች የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው ላይ የሚቀርበው ቅሬታ አግባብ አለመሆኑንና ይህ የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫ እንጂ የግለሰቦች ፍላጎት አለመሆኑን ያብራራሉ። ይህም የሆነው በመንግስትና በግል ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመሩ ትምህርት ቤቶች ውጭ በሸማቾች የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው እንደ አማራጭ የመጡ እንጂ የቅሬታ ምንጭ መሆን የለባቸውም ባይ ናቸው።

ይህ በሌላውም ዓለም የተለመደ ከመሆኑም በተጨማሪ ከአራዳ ውጭ በሌላው ክፍለ ከተማም መኖሩን በመጠቆም የአራዳ ክፍለ ከተማ የተለየ ተደርጎ መወሰድ የለበትም ይላሉ። በአጠቃላይ ግን ለመምህራን፣ ወላጆችና ነዋሪዎች ቅሬታዎች ምላሽ ለመስጠት አማራጮችን ሁሉ እንደሚመለከቱና ለመፍትሄውም እንደሚተጉ ገልፀዋል።

አቶ ጀማል እስማኤል አያይዘውም ትምህርት ቤቱ ወደ መጠጥ ቤት ከተቀየረ አንድ ዓመቱ ነው። እኔ ደግሞ ወደ ቦታው የመጣሁት እነዚህ ሁኔታዎች ከተከሰቱ በኋላ ነው። ይሁንና ትምህርት ቤቱ ያለበት ሁኔታን በወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት በኩል ያልተወደደ እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እስከመሆን ስለመድረሱ ይናገራሉ።

ይህን መረጃ እንደሰማሁ ይላሉ አቶ ጀማል፤ ጉዳዩን ለማጣርትና መማር ማስተማሩ ለምን እንደቆመ ለማጣራት በኮሚቴ ለማየት ሞከርን። መጀመሪያ ትምህርት ቤቱ ዕድሳት በሚል ሰበብ፤ ሥራ ማቆሙንና ይህንን ዕድሳት ለማከናወንም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዚም ቢሮ ቤቱ ቅርስ ስለሆነ ማሳደስ እንደሚፈልግ አሳወቀ። በዚህም የተነሳ እድሳቱ ተደረገ። ይሁንና ከእድሳቱ በኋላ የቢሮ ኃላፊ ሥምና ፊርማ የወጣ ደብዳቤ የተፃፈ ሲሆን መማር ማስተማር ሂደቱን መቀጠል እንደሌለበት አስታወቀ። በቀጣይ ሌላ አገልግሎት የሚሰጥና ጥበቃ የሚያስፈልገው ስለመሆኑም አዘዘ።

ታዲያ ይህን ጉዳይ በመረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ንግግር የጀመሩት አቶ ጀማልና የክፍለ ከተማው የስራ ባልደረቦቻቸው በኋላ ግን ለመማር ማስተማር እክል የሚሆን ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ መቻሉን ይናገራሉ። የሚማሩበት ህፃናት ስለመሆናቸውና ለአደጋ አለመጋለጡን ከሚመለከታቸው አካላትበጋር በመሆን ማረጋገጥ መቻሉንና በረጅም ዓመታት የመጣበት መማር ማስተማር ሂደቱን ማስቀጠል እንደሚቻል በመተማመን በ2015 የትምህርት ዘመን ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር እንዳለበት ሥምምነት መደረጉንና ከሃምሌ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ዝግጅት እያደረገ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

ከሁለት ዓመት በላይ የተዘጋው ትምህርት ቤትም ወደ ሥራው ይግባ በሚለው ሃሳብ ላይ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አሁንም መንግስት የሚሰጠንን አቅጣጫ ይዘን ለመሥራት ችግር የለብንም የሚል ምላሽ እንደነበርም አቶ ጀማል ያስታውሳሉ።

**ሌሳው ፈተና**

ቀድሞ ትምህርት ቤት የነበረው ወደ መጠጥ ቤት ከተቀየረ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ቁሙናው የድራፍትና አልኮል መሸጫ እንጂ ትምህርት ተቋም መሆኑ ተዘንግቷል። ከመሰረተ ልማቶቹ መጓደል በበለጠም አሁን ትምህርት ቤቱ የያዘው ቁመና ወይንም ከውስጥ ያሉት መሰረተ ልማቶች ያው ቀድሞ እንደነበሩት የመዝናኛ ስፍራ ናቸው። ይህን ለማስተካከል የተወሰደው እርምጃም እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ አላመጣም። በተለይም ለህፃናት የሚስማማ ምህዳር በማድረግ ረገድ ብዙ ሥራ የሚቀረው ስለመሆኑና አሁንም ቢሆን 10 ተማሪዎችን ብቻ ይዞ ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታዎች አሉ። ሌላው ቀርቶ ውስጡን መከፋፈልና የህፃናት መማሪያ ስፍራ ማስመሰል አልተቻለም።

በሌላ ጎኑ ደግሞ በወረዳው 120 ህፃናት የሚማሩበት ስፍራ አጥተው ወላጆች በየቀኑ በየትምህርት ጽህፈት ቤቱ ደጅ እየጠኑ ነው። የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ደግሞ እንደ ከተማ አስተዳደር ከመስከረም

# ፍረዱኝ

9 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም ተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት አለበት በሚል መማር መስተማር ሥራውን በይፋ ጀምሯል። በዚህም በርካታ ትምህርት ቤቶች ሥራቸውን በአግባቡ እያከወኑ ነው። ይሁንና ህጻን ዓለም የሚባለው ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ይቅርና ገና አሁንም ተመዝገቡ ብሎ ተማሪዎችን እየቀሰቀሰ ወላጆችንም እያግባባ እና እየወያየ ይገኛል።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 ትምህርት ጽህፈት ኃላፊ አቶ አቶ አበራ አጌና፤ በወረዳው ያለው የአጸደ ህጻናት ፍላጎት እና ያለው ተደራሽነት አይመጣጠንም። ይህንንም ተከትሎ በፈረቃ ለማስተማር የተገደዱባቸው ጊዜያት እንደነበሩም ያስታውሳሉ።

## አወዛጋቢ ደብዳቤዎች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ለትምህርት መስተጓጎልም ሆነ ትምህርት ቤቱ ወደ መጠጥ ቤትነት ሲቀየር የራሱ ድርሻ ያለው ሲሆን፤ አወዛጋቢ የሆኑ ደብዳቤዎችን ሲፅፍ ነበር።

ለአብነትም መስከረም 13 ቀን 2013 ዓ.ም ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ የፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይላል። ጉዳዩ ‹‹የህፃን ዓለም ታሪካዊ ቅርስ ቤትን ይመለከታል›› በሚለው ደብዳቤው፤ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ‹‹የህፃን ዓለም ታሪካዊ ቅርስ ቤትን ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት በመመደብ ጥገናና እድሳት እንዲያገኝ ማድረጉ ይታወሳል።

በመሆኑም ታሪካዊ ቅርስ ቤቱ በቅርስ አዋጅ መሰረት ቀድሞ ይሰጥ የነበረው የመማር ማስተማር አገልግሎት መስጠት ስለማይገባው እና የቅርሱም ደህንነት አደጋ ላይ ስለሚጥል ለቱሪስት መስህብነት አገልግሎት እንዲውል ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲቻል በእናንተ በኩል ታሪካዊ ቅርስ ቤቱን ከሚያስተዳድረው ወረዳ 06 ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር ጋር በመነጋገር ታሪካዊ ቅርስ ቤቱ ነፃ የሚሆንበትን መንገድ እንድታመቻቹ ስንል እናሳውቃለን›› ሲል ለአራዳ ክፍለ ከተማ ባህል፤ ኪነጥበብና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፣ ለባህል ዘርፍ ምትል ቢሮ ኃላፊ ብሎም ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት በግልባጭ አሳውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ለአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እና ለወረዳ 06 አንድነት ቀበሌ11/12 ሸማች ሕብረት ስራ ማህበር በፃፈው ደብዳቤ፤ ‹‹ጉዳዩ የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤት ጥገና እና እድሳት ሥራ መጠናቀቁን ስለመግለፅ›› በሚል የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤትን በጀት በመመደብ ጥገና እና እድሳት እንዲያገኙ መድረጉ ይታወቃል። ታሪካዊ ቅርስ ቤቱ በቢሮ እና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ እየተደረገለት የጥገና ሥራው በባለሙያዎች ተረጋግጦ በመጠናቀቁ የሳይት ርክክብም የጥገና ሥራውን ሲያከናውን ከነበረው ተወለ እና ብርሃን ኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር ተፈጽሟል ይላል።

በመሆኑም ይህ የህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ታሪካዊ ቅርስ ቤት ቀድሞ ይሰጥ የነበረውን የመማር ማስተማር አገልግሎት ለቅርሱ ደህንነትና ጥበቃ ለመማሪያ ተግባር መዋል ስለማይገባው ቅርሶች ተጠግነውና እንክብካቤ ተደርጎላቸው የቅርስ አዋጁ በሚያስቀምጠው አገልግሎት ላይ ብቻ መዋል ስለሚገባቸው የከተማ አስተዳደሩ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ በማንና ለምን አገልግሎት ማዋል እንደሚገባው እስከሚገልጽ ድረስ እንድትጠብቁ ስንል እናሳስባለን›› ሲል በግልባጭ ለቅርስ ጥበቃና ባለስልጣን፣ ለአራዳ ክፍለ ከተማ ባህል፤ ኪነጥበብና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፣ ለህፃን ዓለም አፀደ ህፃናት ትምህርት ቤት፣ ለባህል ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ብሎም ለቅርስ ጥናትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት በደብዳቤዎቹ በግልባጭ ማሳሰቡ ይታወቃል።

ዳሩ ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ እነዚህን ደብዳቤዎች ቢጽፍም እንደተባለው ሆኖ አልተገኘም። ታድሷል የተባለውና ቅርስ የተባለው ቤት እንደተባለው ለቱሪስት መስህብ አልዋለም። ይልቁንም ህፃናት እንዳይማሩበትና የመማር ማስተማር አገልግሎት መስጠት እንደማይችል



**ለህፃናት የሚስማማ ምህዳር በማድረግ ረገድ ብዙ ሥራ የሚቀረው ስለመሆኑና አሁንም ቢሆን 10 ተማሪዎችን ብቻ ይዞ ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታዎች አሉ። ሌላው ቀርቶ ውስጡን መከፋፈልና የህፃናት መማሪያ ስፍራ ማስመሰል አልተቻለም**

በማሳሰብ ትምህርት እንዳይሰጥበት አድርጓል በደብዳቤው መሰረት። በሌላ ጎኑ ግን በዚህ ታሪካዊ ነው ብሎ ባሳወቀውና 300 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎ ዕድሳት በተደረገለት ቤት አዋቂዎችና ወጣቶች ድራፍት ሲጠጡበት እና እንደልባቸው ሲንፈላሰሱበት ማስቆም ሆነ ለመከላከል ያደረገው ጥረት የሚያሳይ መረጃ አላገኘንም። በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊነቱን በአግባቡ ስለመወጣቱ አጠራጣሪ ያደርገዋል።

## አሁናዊ ፈተናዎች

አቶ አበራ አጌና በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 06 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንደሚሉት፤ ትምህርት ቤቱ ከዚህ ቀደም የቆየው መጠጥ ቤት ሆኖ ነው። በዚህም የተነሳ ከውስጥ የነበሩት መማር ማስተማር መሰረተ ልማቶች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ከጥቅም ውጭ የሆኑ ናቸው። በዚህም የተነሳ አዲስ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር አስቸጋሪ ያደርገዋል የሚል እምነት አላቸው።

በተለይም ህንፃው በትምህርት ቤት ‹‹ፎርማት›› የተዘጋጀ እና ህጻናትን ያስተናግድ የነበረ ቢሆንም፤ አሁናዊ ገጽታው ግን መጠጥና የመጠጥ ቤት ተክለ ቁመና የያዘ ነው። ከወንበሮቹ ጀምሮ ለህፃናት የሚመቹ አይደሉም። ይህን ሙሉ ለሙሉ አስተካክሎ ወደ ሥራ ማስገባቱ አስቸጋሪ እንደሚሆንም ይናገራሉ።

የተማሪዎች ምዝገባ ይከናወን ተብሎ ቅስቀሳዎች ቢደረጉም እስካሁን ድረስ ከ10 የማይበልጡ ተማሪዎች ብቻ መመዝገባቸውን ነው የሚናገሩት። ታዲያ ትምህርት ቤቱ ቀደሞ ከነበረው ጥሩ ሥም ዝና ባሻገር በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ 10 ተማሪዎች ብቻ መመዝገባቸው የችግሩን ጥልቀት ያሳያል ይላሉ። አሁንም ቢሆን ችግሩን የመፍታት ፍላጎት ያለ ቢመስልም ለወላጆች፣ ሰራተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች ሁነኛ መፍትሄ ባለመቀመጡ ትምህርት ቤቱን እንደ ቀድሞው ትምህርት ቤት ማሰኘት አስቸጋሪ መሆኑንና ለዚህም ጠንከራ ሥራ መስራት ይጠበቃል የሚል ሃሳብ አላቸው።

አቶ ጀማል እስማኤልም የአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 06 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊን ሃሳብ ይጋራሉ። ትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ሥራውን ካቆመ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ወደ መዝናኛ ሥፍራነት በመቀየሩ መሰረተ ልማቶቹ ተጓድለዋል። በአሁኑ ወቅትም ሙሉ ለሙሉ የተሟላ አይደለም። ይሁንና ከነችግሮቹም ቢሆን ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር አለበት የሚለው ሃሳብ ግን ቅቡል መሆን አለበት ብለው ያምናሉ።

ቀደም ሲል የነበረው የትምህርት ቤቱ ቁሳቁስ ወደ ሌላ ቦታ መጓጓዙንና ይህን የማስመለስ ስራ አልተከናወነም። የተጓደሉትንም ሙሉ ለሙሉ መግዛት አልተቻለም። ትምህርት ቤቱ ወደ ሥራው እንዲመለስ ድጋፍ እናደርጋለን ሲሉ የነበሩ ግለሰቦችና ወላጆችም ከንግግር ባለፈ በተግባር እዚህ ግባ የሚባል ነገር አላደረጉም። ታዲያ ምንም እንኳን ነገሮች የተወሳሰቡ ቢሆንም በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ ሆኖም ቢሆን ግን በ2015 ዓ.ም ተማሪዎችን ተቀብሎ እንዲያስተምር፤ መምህራን በሥራ ገበታቸው ላይ እንዲሰማሩ እንፈልጋለን ባይ ናቸው።

## ቀጣይ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን?

መጀመሪያ ትምህርት ቤቱ ወደ መጠጥ ቤት መቀየሩ በራሱ ትልቅ ስህተት መሆኑን የሚናገሩት አቶ ጀማል፤ ትውልድ ይቀረጽበት የነበረን ተቋም ወደ መጠጥ ቤት መቀየር ከሞራል አኳያም አግባብ አለመሆኑ በመጠቆም፤ ይህ ትምህርት ቤት ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲስተጓጎል ያደረጉ ኃላፊዎችም በሚገባው ልክ ምላሽ ሊሰጡና የሚመለከተው አካል ሁሉ በግልጽ አቋም መውሰድ እንዳለበት ይናገራሉ።

ታዲያ ከትምህርት ቤትነት ወደ መጠጥ ቤት ተቀይሮ የነበረው ትምህርት ቤት፤ በቀጣይ የሚኖረው ዕጣ ፋንታ ተማሪዎችን ተቀብሎ እንደ ቀድሞው ሁሉ ማስተማር ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን በትምህርት ሥርዓቱ መሰረት መምህራንና ሰራተኞችን መብት በመጠበቅ መቀጠል ነው። ይሁንና ተማሪዎችን ተቀብሎ ባያስተምር እንኳን ‹‹በምንም ተዓምር›› ወደ ቀድሞ የመጠጥ ቤትነት እንደማይመለስ ያብራራሉ። ይህ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ውሳኔ ከመሆኑም በተጨማሪ እንደ መንግስትም ተገቢነት የሌለው አቅጣጫ በመሆኑ የባለፈው ስህተት እንደማይደገም አረጋግጠዋል።

የወረዳ 06 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አበራ፤ ወትሮም ከትምህርት ቤትነት ወደ መጠጥ ቤት መቀየሩ በማንኛውም መመዘኛ ትክክል አለመሆኑን በመጠቆም የዚህ ተቋም ዕጣ ፋንታ ትምህርትና ትምህርት ብቻ መሆን አለበት የሚል ምላሽ አላቸው። ለመምህራንና ሠራተኞችም በአግባቡ ምላሽ የሚሰጥ አመራርም መኖር እንዳለበት ይጠቁማሉ። ይህ ካልሆነ ግን አሁንም መፍትሄ አልባ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል። ጉዳዩም ጥሩ ጎኑ ግን፤ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ከተማ አስተዳደሩ ድረስ የሚታወቅ በመሆኑም መፍትሄ ያገኛል የሚል እምነት እንዳላቸው አቶ አበራ ይናገራሉ።

## የከተማዋ ትምህርት ቢሮ....

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ በተደጋጋሚ የእጅ ስልካቸው ላይ የዝግጅት ክፍላችን ቢደውልም በወቅቱ የሥራ መደራረብ የተነሳ ማግኘት ባለመቻሉ የቢሮውን ምላሽ ለማግኘት የተደረገው ጥረት አልተሳካም። ይሁንና የዝግጅት ክፍላችን ጉዳዩን በመከታታል መረጃው እንደተገኘ ዘገባውን የሚያስተላልፍ ይሆናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ለአሸባሪው ትህነግ ሲባል የማይሰራው ዓለምአቀፍ መርህ

ታምራት ተስፋዬ

ሰብአዊ መብቶች ሰዎች ሁሉ ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ ያገኟቸው መብቶች ናቸው።የሰው ልጅ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ ያገኛቸው መሰረታዊ መብቶች አሉት።ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ በህይወት የመኖር መብት፣ ማሰብና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት፣ የመዘዋወር መብት፣ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ሰብአዊ መብቶች ከሌሎች መብቶች የሚለያቸው አራት ዋና ባህሪያት አላቸው።የማይገፈፉ ወይም የማይገረሰሱ (inalienable)፣ተፈጥሮአዊ (Inherent)፣ የማይነጣጠሉ (indivisible) እንዲሁም አለም አቀፋዊነት (universality)መሆናቸውም ልዩ የሚያደርጋቸው ባህሪያት ናቸው።

ለዛሬ ርእሰ ጉዳያችን ሰብአዊ መብቶችን ከሌሎች መብቶች ከሚለያቸው ባህሪያት መካከል አንዱ የሆነው አለም አቀፋዊነት (universality) እንመልከት።ሰብአዊ መብቶች አለም አቀፋዊ ናቸው ማለት ለመላው ሰብአዊ ፍጡር መሰረታዊ ተመሳሳይ ክብርና እውቅና የሚሰጡ ናቸው ማለት ነው።

እነዚህ መብቶች ለሁሉም የዓለም ህዝቦች በሙሉ የተከበሩና እውቅና የተሰጣቸው ሲሆን በማንኛውም መሰረት ልዩነት ሊደረግባቸው የማይችል የሰው ልጆች በሙሉ ሰው በመሆናቸው ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መብቶች ናቸው።ስለሆነም ሰብአዊ መብቶች በዘር፣ በቀለም፣ በሀሃይማኖት፣በፆታ፣በሀብት ደረጃ ወይም በሌላ ልዩነት ሳያደርግ መከበር አለባቸው።

የዓለም የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጠበቃና አርአያ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን በግንባር ቀደምትነት የሚያስቀምጡ ምእራባውያንና አለም አቀፍ ተቃማት ይህ እሳቤና መርህ እወቁና ተግብሩ ሲሉ አጀንዳ አርቅቀው በሰነድ አስደግፈው አቅርበዋል።በየመድረኩ ይህን መርህ ሲደሰኩሩት ይሰማሉ እንጂ ተግባር ላይ ግን የሉበትም።ለዚህ ደግሞ ወቅታዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ በቂ ምስክር ይሰጣል።

እንደሚታወቀው፣ አሻባሪው የሕወሓት ቡድን በህዝብ የጋራ ትግል ስልጣኑን ከተነጠቀ በኋላም የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት በመሰንዘር ኢትዮጵያ ላይ በገሃድ ጦርነት አውጆ መጠነ ሰፊ ጥፋትን አድርሷል።ጦርነቱን ወደ አፋርና ወደ አማራው ክልል በመግፋት በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው በሲቪል ሰዎች ላይ በተለይም በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን እንዲሁም በሲቪል ተቋማት ላይ የመለየት መርህን ባልተከተለ መልኩ ዘግናኝ ኢ ሰብአዊ ጥፋቶችን ፈፅሟል።

ወጣት፣ሴቶች፣ ህጻናትና አዛውንቶችን ጨፍጭፋል።በርካቶችን ለአካል እና ለሥነልቦና ጉዳት ዳርጓል።የቡድኑ ታጣቂዎች በሴቶች ላይ የፈጸሙት ፆታዊና ወሲባዊ ጥቃት ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም።ከ60 እስከ 80 አመት ያስቆጠሩ አረጋዊ ሳይቀር ደፍረዋል።በመፈራረቅ አስገድደው የደፈሯቸው ሴቶች ቁጥር ብዙ ነው።ህፃን ልጆቻቸው ፊት ለፊት የአስገድዶ

**ራሳቸው ካስቀመጡት መርህ በተቃርኖ በአድሎአዊነት እይታ በትግራይ ክልል በርካቶችም አስቸኳይ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የሚነግሩን ሰዎች፣ በሚያሳዝን በሚያሳፍርና በሚያስቆጣ መልኩ የሽብር ቡድኑ በአፋርና በአማራ ክልል ስለፈጸመው ኢ ሰብአዊ ድርጊትና ስለረሃብ ስላጋለጣቸው ዜጎች ትንፍሽ አይሉም**

መድፈር ጥቃት ደርሶባቸው ጥቃቱ በተፈጸመበት ማግስት ታንቀው የሞቱም እንዳሉም የአካባቢው የአይን እማኞች የመሰከሩት ሃቅ ነው።

በንብረት ላይ የተፈጸመ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና ውድመት ስፍር ቁጥር የለውም።በተደራጀ መልኩ በድሃ ህዝብ መዋጮ የተሰሩ በመንግሥት አስተዳደር ተቋማት፣ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት(በተለይ የጤና ተቋማትና የትምህርት ተቋማት) ፣ በግል ንብረቶች እና በንግድ ተቋማት ላይ መጠነ ሰፊ ዘረፋ፣ ገፈፋ እና የንብረት ውድመት ፈፅመዋል።የእምነት ተቋማትን አቃጥለዋል።አወድመዋል።

በመግቢያችን ሰብአዊ መብቶች ከሌሎች መብቶች ከሚለያቸው አራት ዋና ባህሪያት መካከል አለም አቀፋዊነት (universality) መሆኑን አንስተናል።እነዚህ መብቶች ለሁሉም የዓለም ህዝቦች በሙሉ የተከበሩና እውቅና የተሰጣቸው፣ማንኛውም መሰረት ልዩነት ሊደረግባቸው የማይችል፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በሀብት ደረጃ ወይም በሌላ ልዩነት ሳያደርግ መከበር እንዳለባቸው አንስተናል።ይህ መርህ አለም አቀፋዊ እንደመሆኑም የትም ሊተገበር የግድ ይላል።ጥሶ የተገኘ ግለሰብ፣ቡድንም ሆነ አገር ሲገኝም ተጠያቂ ይሆናል።

ይህ ከሆነም ታዲያ ከላይ የጠቀስናቸውን የሰብአዊ መብትና የሰብአዊነት ሕጎች ጥሰት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ሕወሓታዊያን ለተፈጸሙት ጥፋትና ጥሰት ኃላፊነት በመውሰድ፣ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተጠያቂ መሆን አለባቸው ማለት ነው።

ይህ አለም አቀፍ አራተኛ መርህ ግን ሕወሓት ላይ አይሰራም።የአለም የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ጠበቃና አርአያ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን የሚቆጥሩት አገራትና ተቋማትም የሽብር ቡድኑ የእብደት ተግባርና ጥፋት አይታያቸውም።

ጦርነቱ መቆም አለበት በሚል በየትዊተሩ እና ዓለምአቀፍ መድረክ ላይ እርግማን የሚያዘንቡ ተቋማትና ባለስልጣናትም፣በሽብር ቡድኑ ጥፋት የሚሞተው ወገን፤የሚባክነው ሀብት፤የሚወድመውን መሰረተ ልማት መመለከት ፈፅሞ አይፈልጉም።

ቡድኑ የሚፈፅማቸውን በደሎች ሰምተው እንዳልሰማ፣አይተው እንዳለየ፣ገብቷቸው እንዳልገባቸው ሆነዋል።በተጠናና በተቀነባበረ መልኩ የሽብር ቡድኑን የጭካኔ ጥግ የሚያስመሰክሩ ጭፍጨፋዎችን ከማጋለጥ ተቆጥበዋል።ስለሕወሓት ጥፋት ሲነሳ እንደ አምንስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማን ራይትስ ዎች አይነቶቹ ተቋማት የበላቸው ጅብ አይጮህም።

ሌላው ቀርቶ በአለም አቀፍ ደረጃ ህፃናትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለጦርነት መመልመል፣ ማስታጠቅም፣ሰላይነት መጠቀምና ተሳታፊ ማድረግ በአለም አቀፍ ወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑ ተመላክቷል።አሸባሪው ቡድን ህፃናትን ለጦርነት እያሰለፈ መሆኑ በግልፅ አደባባይ እያስተዋሉ እንኳን አይኔን ግንባር ያድርገው ከማለት ውጪ ምንም አልተነፈሱም።

ራሳቸው ካስቀመጡት መርህ በተቃርኖ በአድሎአዊነት እይታ በትግራይ ክልል በርካቶችም አስቸኳይ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው የሚነግሩን ሰዎች፣ በሚያሳዝን በሚያሳፍርና በሚያስቆጣ መልኩ የሽብር ቡድኑ በአፋርና በአማራ ክልል ስለፈጸመው ኢ ሰብአዊ ድርጊትና ለረሃብ ስላጋለጣቸው ዜጎች ትንፍሽ አይሉም።አደባባይ ወጥተው መኮነን ቀርቶ በማህበራዊ ገፃቸው ላይ አንድ መስመር አያሰፍሩም።

ይልቁንም የአሸባሪው ቡድን የጭካኔ ድርጊት ከማውገዝ ይልቅም በሰብዓዊነት ስም ለአሸባሪው ቡድን መተላለፊያ ኮሪደር ስለሚከፈትበት መንገድ ብዙ ሲጨነቁና ሲደክሙ እያየናቸው ነው።ለፖለቲካ ሽሪኮቻቸው ሲሉ ኢሰብዓዊነትን እንደሚያበረታቱ እያሳዩን ይገኛሉ።

በእርግጥ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ተከስተዋል የተባሉ የሰብዓዊ ጥሰቶች መኖራቸው አይካድም።የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ባቋቋሙት ኮሚቴ ጥሰት ስለመፈፀም አለመፈፀሙ ምርመራ አካሂደዋል።

ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ተከስተዋል የተባሉ የሰብዓዊ ጥሰቶችን በጥልቀት በቦታው ተገኝተው በማጥናት ሪፖርት አቅርበዋል።ምክረ ሃሳብም ሰጥቷል።የኢትዮጵያ መንግስትም ከነጉድለቱም ቢሆን ሪፖርቱን ተቀብሎ በምክረ ሃሳቡ መሰረት ችግሮችን ለይቶ ለማረም ወደተግባር ገብቷል።

ይሁን እንጂ ሪፖርቱ የአሸባሪውን ትህነግ ጩኸት ባዶ ያደረገና ለቀለብ ሰፋሪዎቹ ምኞት የሰጠ አልነበረም።ይህን ተከትሎም በጥናት ጭምብል የአሸባሪው ትህነግን ጩኸት የሚያስተጋባና የፈለጉትን ኢትዮጵያ ላይ ጫና የመፍጠር ፍላጎት ለማሳካት ‹‹ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ አለብን በሚል››ሌላ መንገድ ተራምደዋል።

ዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽንም የተልእኮው አስፈፃሚ ሆኖ የቀረበ ሲሆን፤ ኢትዮጵያም በር ከመዝጋት ይልቅ ኮሚሽኑ ምርመራውን እንዲያከናውን አመቺ ከባቢን ፈጥራለች።የኮሚሽኑ ባለሙያዎች የመስክ ምልከታ እንዲያደርጉ ጭምር ሁኔታዎች አመቻችታለች።

ኮሚሽኑ ግን ይህንን ጥሪ ወደ ጎን በመተው እውነተኛ ያልሆነ ጦርነቱ ከተካሄደባቸው አካባቢዎች ቁንፅል ስዕል የያዘና ገለልተኝነትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባና፣ከእውነት በራቀና በተፈበረከ ውሸት የታጨቀ ብቻም ሳይሆን ሚዛናዊነት የጎደለው ሪፖርት ይዞ ብቅ ብሏል።

አድሎአዊ ባልሆነና የአለምአቀፋዊነት (universality)መርህን በጠበቀ መልኩ ሳይሆን እንደተለመደው በፍላጎታቸው በሚያደራጁት የካንጋሮ ፍርድ በመፍረድ፣የሽብር ቡድኑን ኢ ሰብአዊ ድርጊትና ሰብአዊ መብት ጥሰት ሸፈንፈን በማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ በትራቸውን ማሳረፍንም ምርጫቸው አድርገው ታይተዋል።

ይህ ሁሉ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር እንዳትቀጥል የማድረግ ሴራ ነው። እውነት እና ንጋት እንዲሉ ሁሉም ቀኑን ጠብቆ መጋለጡ አይቀርም።በመሰል የተንሸዋረረ እይታ፣ ከመርህና ያፈነገጠ ተፅእኖና በተሳከረ የካንጋሮ ፍርድ ኢትዮጵያና ዜጎቿን ማንበርከክ አንገት ማስደፋትም ፈፅሞ አይቻልም።

# ቡናን በፍጥነት ያገበያዩት አዳዲሶቹ የግብይት አማራጮች

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

በቡናው ዘርፍ በተጠናቀቀው 2014 በጀት አመት ሶስት መቶ ሺ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር ገቢ ተገኝቷል።ይህ ገቢ በቡና የወጪ ንግድ ታሪክ የመጀመሪያ ለመባልም በቅቷል።

ለተገኘው ስኬት በቡና ሻይ ባለስልጣን ከተከናወኑ በርካታ ተግባሮች መካከል በዘርፉ የተካሄደው ሪፎርም፣ ይህን ተከትሎም በቡና ልማቱም ግብይቱም የተከናወኑ ተግባሮች ይጠቀሳሉ።በተለይ በግብይት በኩል ሰፋፊ ውጤታማ ተግባሮች ተከናውነዋል።ሙሉ ለሙሉ ተቀርፏል ብሎ ለማለት ባያስደፍርም፣ የነበሩትን ውስብስብ እና አስቸጋሪ አሰራሮችን መልክ የማስያዝ እና ህግና መመሪያ የተከተለ አሰራር በመዘርጋት በኩል ስኬታማ ስራዎች ተሰርተዋል ማለት የሚያስችል ሁኔታ መኖሩን ባለስልጣኑ ባለፈው ነሀሴ ይዞት ከወጣው መጽሄት የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

አማራጭ የግብይት መንገዶች ወደ ስራ መግባት በግብይት በኩል የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አስችሏል።ለአመታት ሲሰራባቸው የቆዩት ሁለት የግብይት አይነቶች ብቻ እንደነበሩ በቡናና ሻይ ባለስልጣን የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር አቶ ታጠቅ ግርማ ይገልጻሉ።እሳቸው እንደሚሉት፤ ቡና ለውጭ ገበያ የሚቀርብባቸው መንገዶች ኮሜርሻልና ስፔሻሊቲ በመባል ይታወቃሉ።ከሀገሪቱ ቡና አብዛኛው ለውጭ ገበያ የሚቀርበው በኮሜርሻሉ መንገድ ነው። ቡና የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን፣ ከደረጃ ሶስት በላይ ያሉት አራተኛና አምስተኛ ደረጃ ቡናዎች ኮሜርሻል ይባላሉ።እስከ ደረጃ ሶስት ያሉት ደግሞ ስፔሻሊቲ ቡናዎች ናቸው።የስፔሻሊቲው መንገድ አሁን አሁን እየጨመረ መጥቷል፤ ለእዚህም ከጥቂት አመታት ወዲህ በሀገሪቱ በቡና ግብይቱ በኩል የተፈጠሩ አማራጭ ግብይቶች ትልቁን ድርሻ እየተወጡ እንደሚገኙ ዳይሬክተሩ የሚጠቁሙት።

እንደ አቶ ታጠቅ ገለጻ፤ በ2009 አም የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ የወጣ ሲሆን፣ ይህን ለመተግበር ደግሞ በ2011 አም ደንብ ወጥቷል።ይህ አዋጅና ደንብ ስራ ላይ የዋለው በ2012 ነው። አዋጁ ከቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አኳያ የተለያዩ ጉዳዮች የተካተቱበት ሲሆን፣ አንዱም አማራጭ የግብይት ስርአትን ተግባራዊ ማድረግን የተመለከተው ነው።አማራጭ ግብይቶቹ የጀመሩትም ከዚህ በኋላ ነው።

ለግብይት የተባሉትን ለማብራራት የቀድሞውን እና ቀጣይ አማራጭ ግብይት ሆኖ የመጣውን በማነጻጸር አቶ ታጠቅ ሲያብራሩ፣ በፊት አርሶ አደር ያመረተውን ቡና ለመሸጥ ያሉት ሁለት አማራጮች ብቻ እንደነበሩ ያስታውሳሉ።አንዱ አማራጭ ቡናውን ለተደራጀበት ህብረት ስራ ማህበር ማቅረብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አካባቢው ባለው ገበያ ለቡና አቅራቢው/ ሰፕላየር/ ወይም ለነጋዴ ማቅረብ ነበር ሲሉ ያስታውሳሉ።

ይህ አርሶ አደር ምንም አይነት ቡና ያምርት ፈቅዶና ወዶ ያለግዳጅ በሁለቱ አማራጮች ብቻ ቡናውን አቅርቦ ሲሸጥ ኖሯል።አሁን በተፈጠረለት አማራጭ ገበያ ደግሞ አርሶ አደሩ ገበያ አግኝቶ መሸጥ እስከ ቻለ ድረስ ቀጥታ ለኤክስፖርት ማዋል የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።በተለይ ቀጥታ ከአርሶ አደሩ ጋሮ ቡና የሚፈልጉ ካሉና በተለይ ከአርሶ አደሩ ቡና መግዛት የሚችሉበት ሁኔታ ከተመቻቸ አርሶ አደሩ እንደ ነጋዴ ሳይቆጠር ባንኮችና ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በተሰራው ስራ በቀጥታ መላክ የሚችልበት እድል ተፈጥሮለታል።ለእዚህም የቡናና ሻይ ባለስልጣን ትልቁን ድርሻ ወስዷል።

ይህን የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተከትሎ ቀጥታ ቡና ወደ ውጪ ለመላክ ፈቃድ ያወጡ አርሶ አደሮች ከ1500 በላይ ደርሰዋል።በህጉ ማእቀፍ መሰረት ሁለትና ከሁለት ሄክታር በላይ የቡና መሬት ያላቸው አርሶ አደሮች በእዚህ ግብይት መጠቀም ይችላሉ።በዚህም እስከ መቶ የሚደርሱ አርሶ አደሮች ገበያ ውስጥ ገብተው እየላኩ ናቸው፤፡ ይህ አንዱ አማራጭ ነው።

ይህ አማራጭ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፤ በዚህ አማራጭ የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች ገበያ ለሚፈልጉላቸው ሰዎች ከሚከፍሉት ኮሚሽን ወይም የአገልግሎት ክፍያ ውጪ የኤክስፓርት ዋጋውን ቀጥታ በማግኘት መቶ በመቶ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ ።

የግብይት አማራጩ ግን የአርሶ አደሩን ልምድ፣ እውቀትና ግንዛቤ ይጠይቃል የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ ባለስልጣኑ አርሶ አደሮች ይህን ግብይት ለመምራት ትምህርቱም ግንዛቤውም ላይኖራቸው ይችላል በሚል ልጆቻቸውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሙከራዎች እያደረገ ይገኛል።ለአርሶ አደሮቹ ለራሳቸውም በተለያዩ መድረኮች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል።በዚህ በኩል ተቋሙ በዋናነት አቅም ግንባታ ላይ ይሰራል ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ አቶ ታጠቅ ገለጻ፤ ሁለተኛው የልማት ግብይት ትስስር /አውት ሶርስ ስኪም/ የሚባለው ነው።አርሶ አደሩ ያለማል፤ በአካባቢው ያለው ባለሀብትም ያለማል።ይህ አሰራር አልሚ ባለሀብቶች ባለሀብቶች ልምድ ያላቸው ፣ የገበያ ችግር የሌለባቸው ፣ወደማምረት የመጡ ባለሀብቶች እንደመሆናቸው መጠን የገበያ ችግር የለባቸውም ተብሎ ስለሚታሰብ፣ የአካባቢውን አርሶ አደር በኤክስቴንሽን ስራ፣ በግብአት አቅርቦት እያገዙ የተሻለ መጠንና ጥራት ያለው ምርት በማምረት ለእነሱ በተሻለ ዋጋ እንዲያቀርብ ማድረግ የሚያስችል ስርአት ነው። ይህ የአርሶ አደር ባለሀብት ትስስር በሁለቱም ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው።

ሶስተኛዎቹ አማራጮች ቡና ቆልተውና ፈጭተውና አሽገው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶች ናቸው።እነዚህ ድርጅቶች ከአዋጁ በፊት ጥራት ያለው ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቡና መግዛት አይፈቀድላቸውም ነበር። አሁን ግን ይህን ቡና በቀጥታ ከገበያ እንዲገዙ የሚያስችል ስርአት ተዘርግቶ እየተሰራበት ነው።አምራቹም ጥራት ያለው ቡና ለእነዚህ ድርጅቶች መሸጥ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሮለታል።

ሌሎችም አማራጭ ግብይቶች አሉ። አርሶ አደሮች አባል ለሆኑበት የህብረት ስራ ማህበራት ቡናቸውን የሚሸጡበት አማራጭ አላቸው።ሴት አርሶ አደሮች ቀጥታ ለሴት ላኪዎች መሸጥ የሚችሉበት አማራጭ ተፈጥሯል።ይህ እየሆነ ያለው ሴት አርሶ አደሮችን ከማበረታታት አንጻር ብቻ አይደለም፤ ሴት ላኪዎችም እንዲሁ የሚፈልጉትን ቡና ከሴት አርሶ አደሮች እንዲገዙ የሚያስችል ሁኔታም ተመቻችቷል።


አርሶ አደሩ ምርቱን እንደ እስከ አሁኑ ሁሉ ለምርት ገበያ አቅርቦም ለላኪዎች መሸጥ እንደሚችል ጠቅሰው፣ በአጠቃላይ ወደ ስድስትና ሰባት አማራጮች ለአርሶ አደሩ እና ለባለሀብቱ የተመቻቹበት ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን አስታውቀው፣ በቡናው ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶችም በራሳቸው ራሳቸውን የቻሉ አማራጮች መሆናቸውን ነው ያመለከቱት፤ ይህ ሁሉ አሁን በግብይቱ ላይ ለተመዘገበው ውጤት የራሱን ሚና እየተጫወተ ይገኛል ይላሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ሌላው ትልቅ አማራጭ አቅራቢ/ ሰፕላይር/ ላይ የተፈጠረው ነው።አቅራቢ ከአርሶ አደር ቀጥታ የሚገዛ አካል እንደመሆኑ መጠን ቀደም ሲል ምርት ገበያ ገብቶ ለላኪ የሚሸጥበት ሁኔታ ነበር ያለው።ስለዚህ አቅራቢው አካባቢው ካለው ገበያ ከአርሶ አደር ይገዛል፤ በዚህም የታጠበም ሆነ ደረቅ ቡናን አዘጋጅቶ በምርት ገበያ በኩል የሚልክበት አግባብ ነበረው።አሁን ግን ሌላ እድል ተጨምሮለታል፤ያለ ሶስተኛ ወገን ማንም ጣልቃ ሳይገባበት ምርቱን በቀጥታ ለላኪ መሸጥ ይችላል። ምርት ገበያ እንዳለ ሆኖ፣ አቅራቢው በቀጥታ ለላኪ መሸጥ የሚችልበት ሌላ አማራጭ ነው የተፈጠረው።

መነሻ ወይም መነጋገሪያ ዋጋዎች ግን በቡናና ሻይ ባለስልጣን ይቀመጣል፤ በዚህ መነሻ ዋጋ ተነጋግረው አቅራቢና ላኪ ይገበያያሉ ማለት ነው።

ምርት ገበያም የራሱን ስራ እየሰራም በተፈጠሩት የተለያዩ አማራጮች ከ95 በመቶ በላይ የቡና ግብይት በቀጥታ ግብይት ተፈጽሟል ማለት ይቻላል።ምርጫው ተቀምጦላቸዋል፤ አስገዳጅ ሁኔታ የለም፤ አቅራቢው ሲፈልግ ምርት ገበያን እንዲጠቀም፣ ሳይፈልግ ደግሞ ለላኪው የሚሸጥበት አግባብ መመቻቸቱ ላኪው የሚፈልገውን ቡና አይነትና የጥራት ደረጃ ተዋውሎ ቀጥታ ከአቅራቢው እንዲያገኝ ነገሮች ተመቻችተዋል፤ ይህ በመሆኑም ምርቱ ከአርሶ አደር ወደ አቅራቢ ከአቅራቢም በቀጥታ ወደ ላኪ እንዲደርስ የሚያደርግ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ቡናው በቀጥታና በፍጥነት ላኪው እጅ ገባ ማለት ለኤክስፓርት መጠን እድገት የራሱ ሚና እንዲኖረው ያስችላል ያስችላል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ቫልዩ ቼይን / የግብይት ሰንሰለት/ በጨመረ ቁጥር ላኪው አካል ቶሎ ምርቱን አያገኝም፤ ዋጋ የመጠበቅ፣ ጊዜ የመፍጀት ነገሮች ይኖራሉ፤ የግብይት ሰንሰለቱ /ቫልዩ ቼይኑ/ ባጠረ ቁጥር ጊዜ ያጥራል፣ ምርቱ ቶሎ ላኪዎች እጅ ይገባል፤ ስለዚህ ምርቱን ቶሎ ማግኘት ለኤክስፓርት የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ሲሉ ያብራራሉ።ለኤክስፐርት እድገቱ ምርቱ ለኤክስፓርት የሚደርስበት አግባብ ወይም ያጠረ የግብይት ሰንሰለት መፈጠሩ አንድ ምክንያት ነው ተብሎ ይወሰዳል ብለዋል።



በፊት አቅራቢ አቅራቢ ብቻ ሆኖ ብቻ ነበር የሚሰራው።በአዲሱ አሰራር አቅራቢው ልምዱን ባከበተ ቁጥር አቅራቢም ላኪም ሆኖ እንዲሰራ ሁኔታው ተመቻችቶለታል።አቅራቢው በሂደት ላኪ መሆን የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።እንደ አርሶ አደሩ 1500 ላኪ ተፈጥሯል ባልልህም ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ አቅራቢዎች ወደ ላኪነት ተሸጋግረዋል፤ አቅራቢም ላኪም የመሆን እድሉ ተመቻችቷል ሲሉ አቶ ታጠቅ ያብራራሉ።

በሌላ ገጹ ደግሞ ቀደም ሲል ላኪው ከአቅራቢው ቡና ይገዛ እንደነበር ጠቅሰው፣ አሁንም መግዛት ይችላል፤ ይህንን ሲፈልግ በምርት ገበያ በኩል መፈጽም ይችላል፤ ሲፈልግ ደግሞ የአቅራቢነትን ሚናም መጫወት ይችላል ሲሉ ላኪው አቅራቢ ሆኖ ሊሰራ የሚችልበት አሰራር መዘርጋቱን ይናገራሉ፤ ላኪው ራሱ የአቅራቢ ፈቃድ አውጥቶ ታች ወርዶ ከአርሶ አደሩ ለላኪ ድርጅቱ ቡና ገዝቶ መላክ ይችላል።

እነዚህ ነገሮች ላኪው ቡናውን ባጠረ ጊዜ እና በሚፈልገው መጠን እንዲያገኝ አስችለውታል ሲሉ ገልጸው፣ በፊት ላኪ አህት ኩባንያ አቅራቢ አንዲከፍት አይፈቀድም ነበር።ህጉ ይገድብ ነበር።ስራውን ግን በህገወጥ መንገድ ይሰሩት አንደነበር ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ይህ የተከለከለው ህገወጥነትን ለመከከላከል ሲባል ነበር፤ ቡና ለኤክስፓርት የሚመረት ነው፤ ሀገር የውጭ ምንዛሬ ትፈልጋለች፤ ላኪው አቅራቢም ሆኖ ሲሰራ ይህን ለማስተዳደር ያስቸግራል የሚል እሳቤ ፊት ነበር።ቡናው ይባክናል የሚል ሀሳብ ነበር፤ አሁን ግን የማስተዳደር አቅም እያደገ፣ በቴክኖሎጂ እየተደገፈ መጥቷል፣ እህት ኩባንያ ከፍቶ እንዲሰራ የተደረገው የማስተዳደር አቅም ስለተገነባና ብዙም የሚፈጠር ችግር አይኖርም የሚባል ደረጃ ላይ ስለተደረሰ ነው ።ይሄ ላኪ ከእህት ኩባንያው ብቻ እንዲገዛ አይደለም የሚደረገው፤፤ ከሌሎች አቅራቢዎችም መግዛት ይችላል፤፤ ላኪው በተለያዩ አማራጮች ምርቱን የሚያገኝበት ሁኔታ መፈጠሩ ምርቱን ቶሎ እንዲያገኝ እንዲልክ በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል ማለት ይቻላል።

ባለልዩ ጣእም ቡናዎችም የራሳቸው የሆነ ግብይቶች መፍጠራቸውን አቶ ታጠቅ ይጠቅሳሉ።እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በየማህበረሰቡ ዘንድ የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች እንዳሉ ይታወቃል።በዚህ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች ይፍጠራሉ።ለምሳሌ የወይን መጠጥ የጠጪዎቹን ፍላጎት ታሳቢ ያደረጉ የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉት ይታወቃል።ከፍተኛውን የጥራት ደረጃ የያዘ ወይን የሚጠቀሙት በአኗኗራቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው።ሲዘጋጅም እነሱን ታሳቢ ተደርጎ ነው።ልክ እንደዚያ ሁሉ ጥሩ ጣእም ያላቸውን ቡናዎች የሚጠቀሙ ማህበረሰቦች የኑሮ ደረጃ ከፍ ያለ ነው።ባለልዩ ጣእም ቡናዎች በእነዚህ ማህበረሰቦች በእጅጉ ይፈለጋሉ።የባለ ልዩ ጣእም የቡና ውድድሮች በእዚህ አይነት መንገድ ለቡና ግብይቱ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

የግብይት አማራጮች እየጨመሩ መምጣት ለውጭ ገበያ የሚላከው ቡና በፍጥነት እንዲቀርብ አስተዋጽኦ እያደረገ ስለመሆኑ ባለፉት ጥቂት አመታት በቡናው ዘርፍ የተመዘገበው ስኬት ያመለክታል።በተያዘው በጀት አመት በቡናው ዘርፍ የተያዘውን 360 ሺህ ቶን ቡና የመላክና ሁለት ቢሊየን ዶላር የማግኘት እቅድ ለማሳካትም እነዚህ የግብይት መንገዶች ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ስለመሆኑ የተመጣበት መንገድም ያመለክታል።በቀጣይም በግብይቶቹ ላይ ጠንክሮ በመስራት የዘርፉን ተጠቃሚነት ማስቀጠል ይገባል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## አስር ሞልቶ አያውቅም እያሉ፤ ዘጠኙን ማጉደል

**ተገኝ ብሩ**

"ዓለም ዘጠኝ ነው፤ አስር አይሞላ ምን አባቱ!" አድርገው ወይም ላድርገው ብለው በዚህ ዓረፍተ ነገር ብዙዎች ድፍረት ይላበሳሉ። ይሄን ባደርግ ምን ይመጣል? የሚል ሀሳብ በዚህ ዓረፍተ ነገር ያንፀባርቃሉ። የዓለም ዘጠኝ ናት ጨዋታ፤ ሰዎች አንድን ነገር መድፈር አለብኝ፤ ይሄን ባደርገው ምን ይመጣል! ካለው አይብስ! በሚል አንድን ተግባር ለማድረግ ሲያስቡ ይጠቀሙታል። ዓለም ዘጠኝ መሆኑ በብዙዎች ይነሳል።

በእርግጥ አንድ ሁለት ተብሎ ተቆጥሮ ሲያበቃ ዘጠኝ ሞልቶ ከአስር የጎደለው የዓለም ክፍል አይደለም እዚህ ጋር ሚነሳ። ዓለም እዚህ ጋር ኑሮ፣ህይወት በአጠቃላይ ዓለማዊ ሁነት ነው። ዓለም ሁሌም ጎደሎ መሆኑን ለመግለፅ ነው፤ ዓለም ዘጠኝ ነው። አስር አይሞላም፤ የሚሉት ብዙዎቹ። በልጅነቴ ስለ ዓለም ሳይገባኝ ሰዎች አባባሉን ሲሉት ስሰማ ልክ እንደ አፍሪካ ያሉ ሌሎች አህጉራት ተቆጥረው ቁጥራቸው ዘጠኝ ስለሆነ ይመስለኝ ነበር። ዓለም ሰፊ ትርጉም ያለው መሆኑ ቆይቶ ገባኝ።

አለም ግን ጎደሎ መሆን ቢሰለቸው ምን አለ? ጉድለቱ ቀርቶ ሞልቶ ሁኔታዎች ቢለወጡ ማለቴ ነው። በእርግጥም ዓለም ጉድለቷ እውነት ነው። ሙሉ የሆነ ፍስሀ፣ ጉድለት የሌለው ደስታ እክል የሌለው ነፃነት ሙሉ የሆነ ሙሉነት ፈፅሞ የለም። አንዱ ሲሞላ ሌላው ይጎላል። በእርግጥ የዓለም ጉድለትን ተረድቶ ለመሙላት ያለ ልክ መታገል፤ ከአቅም በላይ መወጠርም ተገቢነት የለውም።

ግና ደግሞ የዓለም ዘጠኝነትን አምኖ ተቀብሎ ጎዶሎውን ለማበጀት አለመጣርም ትክክል አይደለም፤ ስንፍና ነው። እንዲሁ በደንብ ሳያስቡበትና ሳያቅዱ ‹‹ምን አባቱ! አስር አይሞላም›› ብሎ በፉከራ ዘጠኙን ለማጉደል መጣር ልክ አይደለም። ምን አባቱ አስር አይሞላ! ብለን የምናደርገው ሁሉ ይበልጥ እንዳያጎለን ያሰጋል።

ዓውዳመት በመጣ ቁጥር ብዙ ሰዎች ወጪው ያሳስበናል። ቤታችን ደምቆ ምግብና መጠጡ ሞልቶ ማየት እፈልጋለን። ታዲያ ለዚህ ሙላት ኪስ መጉደሉ አይቀርም። የሚጎድለው ኪስ ከቶም እንዳያገግምና እንዳይሞላ ተሟጦ ከሆነ ይከብዳል።

በተለይ እንዲህ እንደኛ አገር በዓላት ተደራርበው ሲመጡ ኪሳችንን ማጉደላቸው አይቀርም። አዲስ አመት ነውና የተማሪዎች ትምህርት ቤት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ተነባብረው እኛን ለማራቆት በቀረቡን ጊዜ የአስር አይሞላም ምን አባቱ ጨዋታ አለ የምንለውንም ዘጠኙን ዓለም ሊያጎልብን ይችላል።

ማንም በዓውዳመት መደሰት ይፈልጋል። በዓሉን ከዘመድ አዝማድ ጋር ተሰባስቦ በጥሩ ሁኔታ እየበሉና እየጠጡ ማሳለፍ። ከጎረቤት ጋር ተጠራርቶ አምሮና አጊጦ ማሳለፍ፤ ነገር ግን አውዳመት አውዳመት ሆኖልን በማግስቱ ሂሳብ እንድናሰላ የሚያደርገን፤ እዳ ውስጥ የሚከተን መሆን የለበትም።

ሁሉ ነገር በአቅም ሲሆን መልካም ነው። እንደቤታችን ብናድር አይጨንቀንም። እንደ ኪሳችን ብንደግስ አይጠበንም። በእርግጥ በወጋችን በአቅም መኖርን የሚመክሩ በልክ ማደሩን የሚያበረታቱ ብዙ ብሂሎች አሉን። "አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው፤ ታላቅ ችሎታ ነው" ተብሎም ተነግሮናል።

"ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርም" አይደል የሚባል። አዎ እንደ ቤታችን እንደር፣ እንደ አቅማችን በዓሉን በደስታ እናሳለፍ። ያለንን ለእኛ በሚሆን መልክ አመቻችተን ከአቅማችን ሳንጎድል፤ ከዚያም በላይ ሳንጠራራ ቤታችንን ማድመቅ ይገባል። እንደ ጎረቤታችን ሳይሆን እንደቤታችን ማደር ይገባል።

ጎረቤታችን ፍሪዳ ነው የተጣለው፤ ብለን እኛ ጋር ያለው ቅርጫ ወይም ዶሮ አናርክስ። ወዳጃችን ጋር ኬክ ነው የተቆረሰው ብለን እኛ ቤት የጋገርናት ቂጣ አናጣጥል። ሁለቱም በየራሳቸው ደስታን መፍጠር ይችላሉ። ቤታችን ቢጎልም ፍቅርን መሙላት እንችላለን። በእርሱ ነው ሌላውን መፎካከር። ያልጎደለ ቤተሰባዊ ፍቅር በመላበስ የጎደለን መሙላት ይቻላል።

እዚያኛው ቤት የሌለው ፍቅር እኛ ቤት ላይ ሞልተን ያለችን ትንሽ ነገር ተቃምሰን በፍቅር እንዋል። ወገኖቼ ፍቅር የሞላበት ቤት ላይ ያለ ጉድለት፤ የማይታይና እጅግ የተሰወረ ነው። ከቁስ ይልቅ እሱ ቤታችንን ከሞላ ተጎርሶ ይጠገባል።

አዎ በአቅም ነው ማደር። ዛሬ ላይ አስር አይሞላ ብለን ለወራት የቋጠርነውን ብንፈታ ነገ ብዙ የታሰሩ ጉዳዮች ሲገጥሙን መፍቻ እናጣለን። ዓውዳመቱን ስናስብ የፍስሀ ይሆንልን፤ እኛን የሚያስደስተን ባቅማችን፤ እንደ ቤታችን እናሳልፈው። አብዝተንም ሳንቋጥር ከአቅማችን በላይም የቋጠርናትን ጥሪት ሳንጨርስ አልፎ የሚሄደውን ቀን በአቅማችን ደምቀን በድምቀት እንለፈው።

ስለ ቁጠባ ሲነሳ ሁሌም የሚታወሱኝ የቀድሞ ስራ ባልደረባዬ ናቸው። ሰውየው እጅግ ቆጣቢ ናቸው። ያለምክንያት አንዲት ሳንቲም የማያበኩ። በእርግጥ ቆጣቢነታቸው ባልከፋ ነበር፤ ችግሩ ትንሽ ያበዙታል እንጂ። ለሚበሉትና ለሚጠጡትም በስስት ነው ወጪ የሚያደርጉት። አንዴ በሻይ ሰዓት በመስሪያ ቤታችን መዝናኛ ክበብ ተሰብሰበን በተቀመጥንበት መጥተው ተቀላቅለውን አስተናጋጁን ጠርተው ያሉት ሁሌም እያሰብኩ ፈገግ እላለሁ።

"ና ማን ነህ አስተናጋጅ! ቁርስ በልቻለሁ ግን ርቦኛል። ዓለም አስር ሞልቶ አያውቅም ልብላ ባክህ አንድ ሻይና አንድ ዳቦ አምጣያልኝ" ብለው ሲያዙት ሰማን። አንድ ሻይ በዳቦ ለመብላት የዓለምን ጎደሎነት በማንሳት ሲፎክሩ ነው ፈገግ ያልን። ቀልዱ ብዙ ጊዜ ይባል ስለነበር አብረናቸው የነበርነው ሊያስቁን ፈልገው መስሎን ቀና ብለን አየናቸው። ሰውየው ግን ቆምጨጭ ብለው ነው የሚያወሩት፤ የምራቸውን ነው። ዳቦ በሻይ የመብላት ውሳኔያቸው አጀገኗቸው ተጀንነዋል።

ዞር ብለውም አላዩን፤ እኛን ለማሳቅ የሚሆን ጊዜም ቀልድም የላቸውም። በተለይ ስለወጪ እያወሩ ሊቀልዱ? ኸረ አይታሰብም! ሳያቸው በራሳቸው ጉዳይ ላይ ተጠምደዋል።

ባልደረባችን ወጪን በተመለከተ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያራምዱትን አቋም ስለማውቅ ብዙውን ጊዜ በትዝብት መልክ ነው የማያቸው። በብዙ ጉዳይ ትዝብታችንን እሳቸው ላይ ስለምናበዛ ከመካከላችን ስስታም የሆነ ሲገጥመንና ቁን ቁን ሲልብን "አሁንስ ጋሼ.... መሰልከኝ" እንባባል ነበር።

ወጪ ላይ አብዝቶ ያለአግባብ መዝረክረክ መልካም ልምድ እንዳልሆነ ሁሉ፤ የበዛ ቁጥብነትም መልካም አይደለም። ከልክ በላይ በሆነ ስስት መሰረታዊ የሆነን ፍላጎት ማቀብም ተገቢ አይመስለኝም። ሰው ለሚበላውና ለሚጠጣው ሰስቶ ለምኑ ሊቆጥብ ነው? ባይሆን ለመብላትና ለመጠጣቱ የሚበቃ በቂ ጥሪት መቋጠሩ ላይ ይበርታ እንጂ በሆድ መቋጠር በጎም አይደል፤ የጤና ጉዳትም ያመጣል።

አዎ ሁሉ ነገር በልክና በትክክል እንዲሁም በተገቢ ቦታ ሲሆን ያምራል። ልክ ማወቅ ደግሞ ከእውቀቶች ሁሉ ቀዳሚው ነው።

የመስከረም ወር በዓላት ይበዙበታልና መልካም በዓል!

# ዓለም አቀፍ



## ፊሊፖ ግራንዲ የተመድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ሆነው በድጋሚ ተመረጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት(ተመድ)ጠቅላላ ጉባኤ ጣሊያናዊው ዲፕሎማት ፊሊፖ ግራንዲን የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (ዩኤንኤችሲአር) አድርጎ መረጠ፡፡

ፊሊፖ ግራንዲ ከሐምሌ 1 ቀን 2023 እስከ ታኅሳስ 31 ቀን 2015 የተመድ ኤጀንሲው ከፍተኛ ኮሚሽነር ሆነው በድጋሚ እንደሚያገለግሉ ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

ከፍተኛ ኮሚሽነሩ ፊሊፖ ግራንዲ እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር ጥር 1 ቀን፤2016 ጀምሮ የተመድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (ዩኤንኤችሲአር) ኃላፊ ሆነው ሲያገለግሉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡

ፊሊፖ ግራንዲ በፈረንጆቹ 2016 ወደ ኃላፊነት ሲመጡ የአሁኑ የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በመተካት እንደነበር አይዘነጋም፡፡

በተጨማሪም ፊሊፖ ግራንዲ ከጥር 2010 እስከ መጋቢት 2014 በነበሩ ጊዜያት፤ የተመድ የፍልስጤም ስደተኞች ኤጀንሲን ሲመሩ እንደነበር ይታወሳል፡፡

የተመድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ ማኅበረሰቦችን እና ሀገር አልባ ሰዎችን ለመርዳት እንዲሁም በፈቃደኝነት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ አልያም በተሰደዱበት አካባቢው እንዲቀላቀሉ ወይም ወደ ሦስተኛ ሀገር እንዲሰፍሩ የሚያስችል አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ የተቋቋመ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ነው።

ድርጅቱ፤ ከ27 ሀገራት የመጡ ወደ አንድ ሚሊዮን ገደማ ስደተኞችን ከምታስተናግደው ኢትዮጵያ ጋር በቅርበት እንደሚሠራም የሚታወቅ ነው፡፡

ዩኤንኤችሲአር በግዳጅ የተፈናቀሉና ሀገር አልባ የሆኑ ስደተኞችን የሚረዳ ድርጅት ነው፡፡

በድጋሚ የዚህ ድርጅት መሪ ሆነው የተመረጡት ፊሊፖ ግራንዲ ከሐምሌ 1 ቀን 2023 ጀምሮ ለሁለት ዓመት ተኩል የዩኤንኤችሲአር ኮሚሽነር ሆነው የሚያገለግሉ ይሆናል፡፡



## ፕሬዚዳንት ፑቲን አሜሪካ በጥብቅ ለምትፈልገው ስኖውደን የሩሲያ ዜግነት ሰጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑቲን ለቀድሞ የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት ሠራተኛ እና መረጃ አሳልፎ ለሰጠው ኤድዋርድ ስኖውደን የሩሲያ ዜግነት እንዲሰጠው በፊርማቸው አጽድቀዋል።

ስኖውደን በፈንጆቹ 2013 የአሜሪካ መንግሥት የጀርመኗን መሪ ጨምሮ የ35 ሀገራት መሪዎችን ስልክ እና ኢሜል ላይ ስለላ ማድረጓን አጋልጦ ነበር።

ስኖውደን የሩሲያ ዜግነት ከተሰጣቸው 70 የውጭ ሀገራት ዜጎች መካከል አንዱ መሆኑን ሲጂቲኤን ዘግቧል።


እንደ ዘገባው ኢድዋርድ ስኖውደን የሩሲያ ዜግነት ለማግኘት ያመለከተው በፈረንጆቹ ኅዳር 2020 ነበር።

መረጃ አሳልፎ በመስጠትና እና የመንግሥትን ንብረት በመስረቅ የአሜሪካ የምትፈልገው የ39 ዓመቱ ስኖውደን ከፈረንጆቹ 2013 ጀምሮ በሩሲያ ተጠልሎ ይገኛል። ስኖውደን ከሁለት ዓመት በፊት በሩሲያ ቋሚ የመኖሪያ ፍቃድ አግኝቷል።

ምንም እንኳን የስኖውደን ደጋፊዎች፣ ስኖውደን ለሰዎች የሚቆረቆር ሰው ነው ቢሉም አሜሪካ ግን የአሜሪካ ባለሙያዎችን እና ብሔራዊ ደህንነት ላይ ጉዳት አስከትሏል የሚል ክስ አቅርባለች።

በአሁኑ ወቅት ለበርካታ አስርት ዓመታት በእስር ሊያቆየው የሚችል ክስ በአሜሪካ ተመስርቶበታል።

# ስፖርት





## የዋልያዎቹ በሰባት ጨዋታዎች ያለመሸነፍ ጉዞ

ቦጋለ አበበ

በዓለም አቀፍ እግር ኳስ ማኅበር (ፊፋ) ዕውቅና ካላቸው የውድድር መድረኮች መካከል የወዳጅነት ጨዋታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ለረዥም ዓመታት በፊፋ የወዳጅነት ጨዋታ መርሐ ግብር መሳተፍ ሳይችል የቆየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ)፣ ካለፈው ዓመት ጀምሮ የፕሮግራሙ አካል ሆኖ የወዳጅነት ጨዋታዎችን እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ዋና አሠልጣኝ ሆነው እንዲቀጥሉ የሁለት ዓመት ኮንትራት ከፌዴሬሽኑ ጋር በቅርቡ የተፈራረሙት አሠልጣኝ ውበቱ አባተ፣ ፊፋ ወቅቱን ጠብቆ በሚያከናውናቸው የወዳጅነት ጨዋታዎች ለመሳተፍ ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ ማድረጋቸው ይታወሳል።

በፊፋ የውድድር ፕሮግራም መሠረት ብሔራዊ ቡድኑ መስከረም 13 እና 16 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሱዳን ብሔራዊ ቡድን ጋር በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ሁለት የወዳጅነት ጨዋታዎችን አድርጓል። አሠልጣኝ ውበቱ አባተ ለወዳጅነት ጨዋታዎቹ ከመረጧቸው 23 ተጫዋቾች መካከል በደቡብ አፍሪካው ክለብ ማሜሎዲ ሰንዳውንስ እየተጫወተ የሚገኘው የዋልያዎቹ ወሳኝ አጥቂ አቡበከር ናስር አልተካተተም።

ያም ሆኖ ዋልያዎቹ በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ እየተመሩ ለሰባት ጨዋታዎች ያለመሸነፍ ጉዟቸውን ያረጋገጡበት ውጤት ከትናንት በስቲያ አስመዝግበዋል። ዋልያዎቹ ከሱዳን አቻቸው ጋር በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስታድየም በቀናት ልዩነት ያደረጉትን የወዳጅነት ጨዋታ ሁለት ለሁለት በማጠናቀቅ ባለፉት ሰባት ጨዋታዎች ያለመሸነፍ ጉዞ አድርገዋል።



ዋልያዎቹ ባለፉት ሰባት ጨዋታዎቻቸው ሶስቱን በድል ሲያጠናቅቁ አራቱን አቻ ተለያይተዋል፣

በአቋም መለኪያ ጨዋታው ዋልያዎቹ በመጀመሪያው የጨዋታ ጊዜ ሁለት ግቦች ሲያስቆጥሩ ዳዋ ሆጤሳ አሁንም የቡድኑ የግብ አዳኝ መሆኑን ያስመሰከረበትን አስደናቂ ግብ ከመረብ አሳርፏል። ሌላኛዋን ግብ የመጀመሪያው የጨዋታ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ቸርነት ጉግሳ ማስቆጠር ችሏል። ከቀናት በፊት በመጀመሪያው የአቋም መለኪያ ጨዋታ ዋልያዎቹ ከሱዳን ጋር አንድ ለአንድ ሲለያዩ ሽመልስ በቀለ ብቸኛዋን ግብ ማስቆጠሩ ይታወሳል።

ዋልያዎቹ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ግብጽን 2ለ0 ካሸነፉ በኋላ የወዳጅነት ጨዋታዎችን ጨምሮ በሌሎች ውድድሮች ሰባት ጨዋታዎችን አድርገው አንድም አልተሸነፉም። ከነዚህ ሰባት ጨዋታዎች ሶስቱን ሲያሸንፉም አራቱን በአቻ ውጤት አጠናቀዋል። በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ግብጽን ያሸነፉበት ጨዋታ በጉልህ የሚጠቀስ ሲሆን ደቡብ ሱዳንን እንዲሁም ሩዋንዳን በቻን ማጣሪያ 5ለ0 እንዲሁም 1ለ0 ማሸነፋቸው ይታወቃል። በአቻ ውጤት ካጠናቀቋቸው አራት ጨዋታዎች መካከል በዚሁ የቻን ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታዎች ከደቡብ ሱዳንና ከሩዋንዳ ጋር 0ለ0 የተለያዩበትና ሰሞኑን ከሱዳን ጋር በሁለት የወዳጅነት ጨዋታዎች 1 ለ 1 እና 2 ለ 2 ያጠናቀቁበት ተጠቃሽ ናቸው።

ዋልያዎቹ ባለፉት አምስት ወራት ያለመሸነፍ ክብረወሰናቸው ጥሩ የሚባል ነው። ቁጥራዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ግን ዋልያዎቹ በ2022 የውድድር ዓመት በተለይም በወዳጅነት ጨዋታዎች(የሱዳኑን ሳይጨምር) አፈጻጸማቸው መካከለኛ ደረጃ የሚሰጠው ነው። በዚህ ረገድ ሁለት ጨዋታ በማሸነፍ፣ አራት አቻ በማጠናቀቅና አራት በመሸነፍ አጠናቀዋል። ይህም የዋልያዎቹን የወዳጅነት ጨዋታዎች የማሸነፍ አፈጻጸም ሃያ በመቶ እንደሆነ ያመላክታል። በነዚህ ጨዋታዎች ዋልያዎቹ በሜዳቸውም ከሜዳቸው ውጪም በሚያደርጉት ጨዋታ ያለመሸነፍ ክብረወሰናቸው ጥሩ ሊባል የሚችል ነው። ለዚህም በሜዳቸው አንድ ጨዋታ ሲያሸንፉ አንድ ብቻ ተሸንፈው ሶስት ጨዋታ አቻ የተለያዩበት ቁጥራዊ መረጃ ማሳያ ነው። ከሜዳቸው ውጪም አንድ በማሸነፍ፣ አንድ አቻ በማጠናቀቅና ሶስት በመሸነፍ አጠናቀዋል።

ዋልያዎቹ በውድድር ዓመቱ ከሱዳን ጋር ያደረጉትን ሳይጨምር በአስራ አንድ የወዳጅነት ጨዋታዎች አስራ አንድ ግቦችን ከመረብ ሲያሳርፉ አስራ አራት ግቦችን ደግሞ አስተናግደዋል። በነዚህ ጨዋታዎችም በአማካኝ በስልሳ አራት ደቂቃዎች በአማካኝ አንድ ግብ ያስተናግዳሉ ማለት ነው። በእያንዳንዱ ጨዋታም በአማካኝ 1.4 ግብ ያስተናግዳሉ እንደማለት ነው።


## በጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
## የተተው ዕቃዎች ግልፅ ጨረታ ቁጥር ግ15/2015 ጨረታ ማስታወቂያ

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስመጪዎችን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 ወይም/እና አንቀፅ 156 ንዑስ አንቀፅ 4 ወይም/ እና አንቀፅ 169 ንዑስ አንቀፅ 2 (በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻሉ ሆኖ) ወይም/እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀፅ 168 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ዕቃቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ባለመውሰዳቸው ወይም የጉምሩክ ህግን በመተላለፋቸው ምክንያት ዕቃዎቹ እንደተተው ወይም እንደተወረሱ ተቆጥረዋል፡፡ ስለሆነም የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተተው ወይም የተወረሱ ዕቃዎችን በገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ኮሚሽን በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ስለሚወገዱበት ሥርዓት ባወጣው መመሪያ ቁጥር 167/2012 አንቀጽ 9 መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ማለትም (Branded Children Sports Shoes (ብራንድ ደረጃ ያለው የልጆች ጫማ) ፤ Wall Paper (በቀለማት ያጌጣ የግድግዳ ወረቀት የቤልጂየም ስሪት) Copper Welding wire Turkey origin (የመበየጃ ሽቦ የቱርክ ስሪት) 6gm/pcs Instant Flavoured Powder for drink SunJus Brand Turkey origin (ለመጠጥ የሚሆኑ የጁስ ዱቄት የቱርክ ስሪት) Tunaylar Tech Electronic Truck Scale Compete Set 80 ton Turkey origin (መኪና ከነጭነቱ የሚመዝን ኤሌክትሮኒክ የምድር ሚዛን የቱርክ ስሪት) Used Iron Steam (ያገለገለ የልብስ ካውያን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጫረት የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር፣ ዓይነት ብዛት፣ የጨረታ ሠነድ እና መመሪያ መግለጫ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ዘወትር ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 6:00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 እስከ ቀኑ 10፡30 እና ዓርብ ከጠዋት 2:00 እስከ ቀኑ 5፡00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7:30 እስከ ቀኑ 10፡30 እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5:30 የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) በመክፈል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ሂሳቦች ቡድን መውሰድ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር በዘርፉ የፀና ንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው ሆኖም ግምታዊ ዋጋቸው ከብር 500,000.00 በታች የሆኑ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሠርተፍኬት ማቅረብ ሳያስፈልግ መወዳደር ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል። ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ አሸናፊው እንደታወቀ በ3 (ሶስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ዋጋ ላይ የሚታሰብላቸው ይሆናል፡፡ተጫራቾች የሚያስይዙት CPO በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስም ETHIOPIAN CUSTOMS COMMISSION MODJO BRANCH OFFCE በሚል ሲሆን የግል ባንክ ከሆነ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቅርንጫፎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሆነ ደግሞ ከአዲስ አበባ አዳማ እና ሞጆ ቅርንጫፎች መዘጋጀት አለበት ተሳታፊዎች ዋጋ መሙላት የሚችሉት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው ማህተም ያረፈበት ሠነድ ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ በመግዛት የሚወዳደሩበትን ዕቃ አስቀድሞ ማየት ያለባቸው ሲሆን ዕቃውን ሳያዩ ለሚሞሉት ዋጋ ቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡
5. የግልፅ ጨረታ ተሳታፊ ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃዎች ለመግዛት የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ፤ የሞሉበት ሠነድ በተራ ቁጥር 2 የተገለፁትን ማስረጃዎች ኮፒ እና ያቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO በኤንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ8 ተከታታይ ቀናት ጠዋት 4፡45 ድረስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል፡፡
6. የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
7. የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣበት ቀንን ጨምሮ በ8ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4:45 ታሽጐ በዚሁ ዕለት ጠዋቱ 5፡00 ላይ ተጫራቾቹ ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ በአዘጋጀው ቢሮ ውስጥ ይከፈታል፡፡
8. ማንኛውም በግልጽ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይንም የሌላ ተጫራቾችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም፡፡
9. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ጨረታውን ለማሸነፍ ሲል መደለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ይወገዳል፡፡ ጨረታው ከተካሄደ በኋላም ቢሆን ጨረታ አሸናፊው ጨረታውን ያሸነፈው በህገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ የጨረታው ውጤት ይሰረዛል፡፡
10. ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤት እና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም፡፡
11.ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ እራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይቻልም፡፡
12.ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡
13.የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፋቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለበት በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ያስያዙት ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል። ያሸነፉት ዕቃም በድጋሚ ለጨረታ ሽያጭ ይቀርባል፡፡
14. በተራ ቁጥር 12 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ ዕቃውን ያላነሳ/ያልተረከበ እንደሆነ ለሚቆይበት ለተጨማሪ ጊዜ የመጋዘን ከራይ ይከፍላል፡፡ ሆኖም ዕቃው በ2 (ሁለት) ወራት ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በጨረታ ሽያጭ ይወገዳል፡፡
15. አሸናፊው ተጫራች ዕቃዎችን ለመረከብና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ ራሱ ይሸፍናል፡፡
16. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ የአቀረበውን ዕቃ ብዛት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ሙሉ መብት አለው
17.ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከአገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡
18. ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 022-236-90-94 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት